




# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# የመምህር መምሪያ



ሦስተኛ ክፍል የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ

አዘጋጆች፡-

መሣይ ለማ (MA)
አማኑኤል ዮናስ (MA)
ፀሐይ ደረሰ (MA)

አርታዒ፡-

ይኄይስ ባንታየሁ (MA)

የጥራት ክትትል፡-

እንግዳ ዘውዴ (ዶ/ር)
አወቀ ጸጋዬ (MA)

የማጣሪያ ንባብ፡-

ኢሳይያስ ይልማ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና
በዲላ ትምህርት ኮሌጅ የቴክኒክ ድጋፍ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው፡፡

# ማውጫ


መግቢያ ........ V

ምእራፍ አንድ ........ 1

ልዩ ልዩ ድምጾች ........ 1

ምእራፍ ሁለት ፊደል በጨዋታ ........ 21

ምዕራፍ ሦስት ........ 33

**እራስን ማስተዋወቅ** ........ 33

ምዕራፍ አራት ........ 42

**ትምህርት ቤቴ** ........ 42

ምዕራፍ አምስት ........ 51

አካባቢያችን ........ 51

ምእራፍ ስድስት ........ 62

**የግልንጽህና አጠባበቅ** ........ 62

ምዕራፍ ሰባት ሥነ ምግባር ........ 73

ምዕራፍ ስምንት የአመጋገብ ስርዓት ........ 84

ምዕራፍ ዘጠኝ ........ 9

**የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ** ........ 9

ምእራፍ አስር ........ 20

ተላላፊ በሽታዎች ........ 20

የክሒል ዓይነቶት ........ 31

ማዳመጥ ........ 31

መናገር/ንግግር ........ 33

ማንበብ ........ 34

ጽህፈት ........ 36

ቃላት ........ 37

ሰዋስው ........ 38

## መግቢያ

በሀገራችን አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ በትምህርትነት የሚሰጥበትን ዓላማመሠረት በማድረግ ሶስተኛን ክፍል የአማርኛ ቋንቋን መማሪያ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል፡፡በዚህም በደረጃው ከተመረጡት የትምህርት ይዘቶች አኳያ የተማሪዎችን ዳህራዊ እወቀት የትምህርትና የእድሜ ደረጃ ባህል፣ጤና፣አካባቢ እንክብካቤን ሥነ ምግባርን እንዲሁም የተመደበውን የትምህርት ሰዓት የሚመጥኑ የትምህርት ልምዶች በተገቢው መንገድ ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡

ይህ የሶስተኛ ክፍል አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍ እያንዳንዱ ምእራፍ በክፍል ተመድቦ ከምእራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች ዝርዝር ይዘቶች የትምህርቱን አቀራረብ የሚጠቁሙና የማዳመጥ ክሂልን ለማለማመድ የሚያስችሉ ምንባቦች መልመጃዎች ተካተዋል፡፡በመጨረሻም ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ በመርጃ መሳሪያነት ሊቀርቡ የሚችሉ መሳሪያዎች ቀርበዋል፡ ፡ለመገምገም የሚያስችሉ ስልቶች በየመልመጃዎቹ ቀርበዋል በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች ከነመልሳቸው ቀርበዋል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ መጽሐፍ የተጠቆሙት የትምህርት አቀራረብ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችና የግምገማ ስልቶች ለመምህሩእንደመነሻ እንዲሆኑ በሚል የቀረቡ እንጂ መምህራኑ የራሳቸውን ልምድና ፈጠራ እናዳይጠቀሙ የሚያግድ አይደለም፡፡ይልቁንም የትምህርቱ አቀራረብ የመርጃ መሳሪያ አመራረጥና አጠቃቀም እንዲሁም የመልመጃ መልሶች የተማሪዎችን አካባቢ መሠረት ተደርገው ሊቀርቡ እንደሚችሉ ማስገንዘብ እንወዳለን፡፡

## ምእራፍ አንድ

### ልዩ ልዩ ድምጾች

<u>የሚጠበቁ ውጤቶች</u>

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የተለያዩ የእንስሳ ድምጾችን ይለያሉ
- የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪዎችን ስም ይናገራሉ
- የቤት እንስሳት ስሞችን ይጠራሉ
- የቁሳቁስ ስሞችን ይናገራሉ
- አልባሳትን በዓይነት ይናገራሉ
- ትእዛዛትን አዳምጠው ይፈጽማሉ ፊደላትን ያነባሉ
- ፊደላትን ይጽፋሉ
- ስእሎችን ከቃላት ጋር ያዛምዳሉ

## አዳምጦ መናገር

የእንስሳትን ድምጽ በማዳመጥ ስማቸውን መግለጽ

**ሀ.ማዳመጥ**

- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪዎችን በማዳመጥ ስማቸውን ይለያሉ

**ለ. መናገር**

- ትምህርት፣ ሶስት ሥዕሉን በማየት የእንስሳት ስሞችን ይናገራሉ
- ትምህርት አራት የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን ስም ይናገራሉ
- ትምህር አምስት የአልባሳትን ዓይነት ይናገራሉ
- ትምህርት ስድስት ትእዛዝን አዳምጦ ይተገብራሉ

**ሐ. ማንበብ**

- ሰባተኛ ሳምንት ባለሁለት እግር ሆሄያትን ያነባሉ
- ስምንተኛ ሳምንት ሆሄያትን ከስእሎች ጋር ያዛምዳሉ
- ዘጠነኛ ሳምንት ተመሳሳይ ቅርጽ ላቸውን ሆሄያትን ያዛምዳሉ

**መ.መጻፍ**

- አስረኛ ሳምንት ባለሁለት እግር ፊደላትን ከነዘሮቻቸው እያነበባችሁ ይጽፋሉ
- አስራ አንደኛ ሳምንት በ ሰ ሸ የሚጀምሩ ቃላትን ይጽፋሉ
- አስራ ሁለተኛ ሳምንትቃላትን ከቁስ ጋር በማዛመድ ይጽፋሉ

# ትምህርት አንድ

## አዳምጦ መናገር

የእንስሳ ድምጽን በማዳመጥ ስማቸውን መግለጽ

1. **የማነቃቂያ ተግባር**

   አዳምጦ መረዳት ክፍለ ትምህርት በቀጥታ ከመግባትዎ በፊት በአካባቢቸው የሚያውቋቸውን የእንስሳ ድምጽ በማስመሰል እንዲያሰሙ ወይም በሞባይል ያሰሟቸው

2. **አቅርቦት**

   መምህር/ት ተማሪዎች በመማሪያ መጽሀፋቸው በሥዕል የቀረቡትን እንስሳት ስእሎች እንዲመለከቱና ስማቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ

   ቀጥሎም የእንስሳቱን ስም በተደጋጋሚ በመጥራት ተማሪዎቹ ሥዕሉን በመመልከት እርስዎ ሲጠሩት አዳምጠው እንዲጠሩ ያበረታቷቸው

   ቀጥሎ ተማሪዎች የመናገር ክህሎታቸውን ሊያዳብርላቸው ስለሚችል የእንስሳትን ወይም የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያውን የመጀመሪያ ፊደል በመጥራት አሟልተው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው

3. **መልመጃዎች**

   መምህር/ት የእንስሳውን የመጀመሪያ ፊደል በመናገር ድምጻቸውን በማሰማት

   በመመሪያ ቁጥር 1 የቀረበውን ልምምድ በተመለከተ በመጀመሪያ ተማሪዎችን በጥንድ በጥንድ በማስቀመጥ የዳመጡት የየትኛው እንስሳ ድምጽእንደሆነ ወይም የየትኛው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ እንደሆነና እንስሳቱ ምን አይነት ጥቅም እንደሚሰጡ እርስ በእርስ እንዲወያዩ አድርጉ

በመጨረሻም ቀጥሎ የቀረቡትን የቤት እንስሳት ስሞችና የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ እርስዎ እያነበቡ ተማሪዎች እርስዎን አዳምጠው ያለማምዷቸው ተማሪዎቹ እንስሳቱን በቪዲዮ በፎቶ ወይም የሙዚቃ መሳሪያዎቹን ከተቻለ በአካል በማሳየት ስማቸውን እንዲናገሩ በመጠየቅና ማስተካከያ በመስጠት ማጠናከር ያስፈልጋል"

| | |
|---|---|
| ውሻ | ክራር |
| ድመት | ዋሽንት |
| በግ | ጥሩምባ |
| ከበሮ | ማሲንቆ |

በመጨረሻም በቤታቸው ወይም በአካባቢያቸው የሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዲያዩና ቤተሰቦቻቸውን እንዲያሳዩና እንዲጠይቁ መመሪያ ይስጧቸው።

## ትምህርት ሁለት

### አዳምጦ ስማቸውን መለየት

**1. የማነቃቂያ ተግባር**

ትምህርት ሁለትን በተመለከተ በስልክ የባሕላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ለተማሪዎች  በማሰማት ድምጾቹን እንዲለዩ እና እንዲናገሩ ያድርጉ

2.**አቅርቦት**

የትምህርቱን አቅርቦት በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን

ስእሎች ተመልክተው ተማሪዎቹ ምን እየተከናወነ እንዳለ እንዲያስረዱ

ያድርጉ

ምሳሌ 1

በከበሮ ምን እየተደረገ ነው? በማለት በምሳሌው መሠረት እንዲሰሩ

ያድርጓቸው

**ትምህርት ሶስት**

1. **ማነቃቂያ**

እናንተ የትኛውን እንስሳ ታውቃላችሁ? በማለት ይጠይቋቸው

ለሁሉም የጋራ ስለሆነችው ላም ጥቅም እንዲናገሩ ያነሳሷቸው ።

በሚናገሩበት ጊዜ ልጆቹ እንዳይሸማቀቁ የእርስዎ እገዛ ያስፈልጋቸዋል፡፡

በነጻነት እንዲነጋገሩ የሚሸማቀቅ ተማሪ እንዳይኖር ያግዟቸው፡፡

2. **አቅርቦት**

በመጀመሪያ እርስዎ ስለ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ጠቀሜታ በዝርዝር ይንገሯቸው ።

እያንዳንዱ ተማሪ የሚያውቀው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ይጠይቋቸው፡

ተማሪዎቹም በቤታቸው ወይም በአካባቢያቸው ስለሚያውቋቸው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ እንዲናገሩ ያግዟቸው ይህንን ተግባር ሲፈጽሙ ለተማሪዎች ነጻነት

ይስጧቸው፡፡ የመግለጽ ችግር ሲያስተውሉ ይደግፏቸው፡፡

3. **መልመጃ**

መልመጃዎችን ለማሰራት በመጀመሪያ እረስዎ ትእዛዛቱን በማንበብና

በስእላዊ መረጃ በመደገፍ ተግባሩን እንዲለማመዱ ያድርጓቸው፡፡ምስሉን

እየተመለከቱ ሲሰሩ እየተዘዋወሩ ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

1. ሥዕሉን በማየት የእንስሳቱን ስም ግለጹ



**ክፍለ ትምህርት አራት**

**የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ አይነት**

1. **ማነቃቂያ**

   ይህን ክፍለ ትምህርት ለመጀመር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ስለመገልገያ እቃዎቹ ቀለል ያለ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ቡና በምን ይወቀጣል? እያሉ ይጠይቋቸውና የተማሪውን መልስ ይጠብቁ፡- ምላሹ / በዘነዘና፡፡

2. **አቅርቦት**

በመማሪያ መጻፋቸው የተቀመጡትን ሥዕሎች በቢጤ በመሆን እንዲመለከቱና የቁሱን ምንነት ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፤ ተማሪዎቹ እርስ በእርስ እንዲወያዩና ሀሳብ እንዲለዋወጡ ያግዟቸው፡፡ እርስዎ ውይይታቸውን ይከታተሉ፡፡በምሳሌም ያሳዩአቸው፡፡

መምህር፡- ቆሎ በሳህን ይቀርባል

በሲኒ ቡና ይጠጣል፡፡ እያሉ ማሳየት ይኖርብዎታል፡፡

3.**መልመጃዎች ሥዕል**



ከላይ የቀረቡትን ቁሶች ምንነታቸውን ግለጹ

ለምን አገልግሎት ይውላሉ ? በሲኒ ቡና ይጠጣል

በምጣድ ምን ይደረጋል - ቡና ይቆላል

ማራገቢያ ለምን ያገለግላል ፡-እያሉ ተማሪዎችን ይጠይቁና ወጥተው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ለምሳሌ ከሰል ለማቀጣጠል

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## ስለ አልባሳት መናገር

### 1. ማነቃቂያ ተግባር

በመጀመሪያ እርስዎ ስለለበሱት ልብስና ስለተጫሙት ጫማ

ይጠይቋቸው እርስዎ እኔ-------ለብሻለሁ እያሉ ይንገሯቸው

በመቀጠል እኔ የለበስኩት ምንድነው? በማለት ጠይቀዋቸው

እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡

ኮት ፣ሸሚዝ፣ሹራብ…እያሉ ሊመልሱ ይችላሉ፡፡

### 2. አቅርቦት

መምህር በተማሪው መጽሐፍ በሥዕል የተቀመጡትን አልባሳት ዓይነት ለመግለጽ እንዲመች ከተማሪዎች ደንብ ልብስ መጀመር ይችላሉ፡፡በደንብ ልብስቸው ሹራብ ካለ ሸሚዝ፣ሱሪ፣ጫማ፣ጉርድ፣ ቁምጣ የመሳሰሉት አንድ ተማሪ በማሥነሳት ልብሱን በእጅዎ እየነኩ ይጠይቋቸው እንዲመልሱም ያበረታቷቸው



መምህር ለተማሪዎቹ በአማርኛ አፋቸውን ያልፈቱ ሊሆኑ ስለሚችሉ እንዳይሸማቀቁ ጥንቃቄ ያድርጉ ፡፡

መልመጃዎች

1. ስእሎቹን በማየት የአልባሳቱን ዓይነት ግለጹ በመጀመሪያ ተማሪዎቹ ጥንድ ጥንድ በመሆን ሥዕሉን ይመልከቱ፡፡







ውድ መምህር/ት የተማሪውን መጽሐፍ በመያዝ ሥዕሉ ምን ያሳያል በማለት ይጤቋቸው?

ለምሳሌ፡-

ሥዕል 1

ቀሚስን በመንካት ይህ ምንድነው ይበሉ?

ተማሪዎችም <u>ቀሚስ</u> ብለው ይመልሳሉ እርስዎም ተማሪውን በተናጥል በማሥነሳት በጋራ ያሉትን ይጠይቁ ተማሪው ሲመልስ ያበረታቱ፡፡መምህር ተግባሩን ለእርስዎ በሚመችና ግብአት ማግኘት በሚችሉበት መንገድ ማሳየት ይኖርብዎታል፡፡

# ትምህርት ስድስት

## ትእዛዝን አዳምጦ መተግበር

1. **ማነቃቂያ ተግባር**

ተማሪዎች እንዲነቃቁ ለእርስዎ አመቺ በሆነ መንገድ ሥዕል በማሳየት ተማሪዎቹን በማነሳሳት የተለያዩ ተግባራትን በማድረግ በማዘዝ እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡ወደዋናው ተግባር እንዲገቡ ያግዛል፡፡


2. **<u>አቅርቦት</u>**

በመማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን ተግባራት ለማሰራት ተማሪዎችን በቡድን ያስቀምጡና በመማሪያ መጽሀፋቸው ያለውን ሥዕል በመመልከት ምን አይነት ተግባር እያከናወኑ እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡ተማሪዎችም ሥዕሉን እያዩ እዲመልሱ ያድርጉ፡፡









## ክፍለ ትምህርት ሰባት

### ፊደላትን ማንበብ

1. ማነቃቂያ፡-

   መምህር- ተማሪዎች የፊደል መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርጉ ባዳመጡት ፊደል ሚጀምር ቃል ያንብቡ

   ለምሳሌ፡- በግ የሚል መዝሙር ያዳምጡ

2. አቅርቦት

   መምህር እርስዎ ፊደላቱን በእርጋታ ያንብቡላቸው ከዚያም ተማሪዎች ባዳመጡት መሠረት ፊደሉን ያነባሉ፡፤ፊደሉን የሚወክል ምልክት በሰሌዳ ላይ ይጻፉ በዚያ መሠረት ያነበቡትን ፊደል በደብተራቸው ይጻፉ፡፡መምህር ፊደላቱን በሚጽፉበት ጊዜ ጥብቅ ክትል ያድርጉ፡፡ደጋግመው እንዲጠሩና እንዲያነቡ ይርዷቸው፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |

መልመጃዎች

በ፣ሰ፣ሸ፣ከ፣ የሚጀምሩ ፊደላትን ያንብቡ  መምህር ከላይ በ፣ሰ፣ሸ የሚጀምሩ ቃላትን እርስዎ ያንብቡላቸው በመከተል እነርሱ ያንብቡ፡፡

በ ቡ ቢ ባ ቤ ብ ቦ

ሰ ሱ ሲሳ ሴ ስ ሶ

ሸ ሹ ሺ ሻ ሼ ሽ ሾ

ከ ኩ ኪ ካኬ ክ ኮ

ለ ሉሊላሌ ልሎ

*መልመጃዎች*

በ፣በግ በ፣በሬ በ፣ በር በ፣በግ

ሰ፣ሰበሰበ ሰ፣ ሰበረ ሰ፣ሰባ

ሸ ሸጠ፣ ሸ ሸመተ፣ ሸ ሸፈነ የሚሉ ቃላትን ያንብቡላቸው እርስዎን ተከትለው እነሱም ያንብቡ።

## ክፍለ ትምህርት ስምንት

1. **ማነቃቂያ፡-**

   በ፣ሰ፣ሸ፣ከፊደል የሚጀምሩ ቃላትን እርስዎ በመጥራት እነሱም እንዲጠሩ ያድርጉ።በመዝሙር መልክ ቃላቶቹን ደጋግመው እንዲዘምሩ ካደረጉ በኋላ ጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፉ።

2. **አቅርቦት**

   መምህር ቀጥሎ የቀረቡትን ሆሄያት በእርጋታ ያንብቡላቸው ያነበቡላቸውን ቃላት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ።ደጋግመው ያንብቡላቸው ትእዛዛቱንም በደንብ ይግለጹላቸው ።

**ትእዛዝ ፡-** **የሚከተሉትን ቃላት ጻፉ**

| | |
|---|---|
| በሶ | ሳሳ |
| ሰባ | ባሰ |
| ባሰ | ሸሸ |
| ሲሶ | ባባ |

**መልመጃዎች**

በ"ሀ"ስር የቀረቡትን ስእሎች በ፣፣ለ..ስር ከቀረቡት ሆሄያት ጋር አዛምዱ በማለት ግልጽ ትእዛዝ ይስጧቸው ስእሎቹን ከመማሪያ መጽሀፋቸው እያዩ ከመጀመሪያው ፊደላት ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ

ሥዕል ባ- ባትሪ

ሸ - ሸዶ ሸ -ሸሚዝ ሰ - ሰዓት ናቸው፡፡

መስራታቸውን በመከታተል ወዲያውኑ ግብረ መልስ ይስጡ፡፡ተመሳሳይ ተግባራትንም በቤታቸው እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡

**ክፍለ ትህርት ዘጠኝ**

**አላማ፡- በ፣ሰ፣ሸ፣ከሆሄያትን ከነዘሮቻቸው ማንበብ**

የማነቃቂያ ተግባር

መምህር በቀለ፣ከበደ፣ሰለሞን ወይም በፊደሎቹ ዘር ሚጀምር ስም ያለው ተማሪ በማሥነሳት ስሙን እንዲጽፍ በማድረግ የሆሄያቱን ዘሮች በማዛመድ ይለማመዱ፡፡

አቅርቦት

መምህር/ት በዚህ ትምህርት ክፍል በተማሪው መጽፍ በአቅርቦት ስር የቀረቡትን ሆሄያት እርስዎ አንብበውና ጽፈው ካሳዩዋቸው በኋላ ተማሪዎች እንዲያነቡና እንዲጽፉ የግዟቸው፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |

ከ - የመሳሰሉት ሆሄያትን ደጋግመው በማንበብ እንዲጽፉ ያድርጉ መጻፋቸውንም በመከታተል ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

**መልመጃዎች**

መምህር በ፣ሰ፣ሸ፣ ከ ሆሄት ዘሮችን ደጋግመው እንዲጽፉ ያድርጓቸው ሆሄያቱን ሲጽፉ እዘመሩ (እየተናገሩ)እርስዎም እደገፏቸው መሆን አለበት፡፡

## ክፍለ ትምህርት አስር

## የቃላት ምሥረታ

1. **የማነቃቂያ ተግባር**

መምህር/ት ቀጥሎ የቀረበውን ቡሄ በሉ የልጆች ጨዋታ እንዲለማመዱ ያድርጉ

ቡሄ በሉ ልጆቹ ሁሉ

ቡሄ መጣ ያ መላጣ

ቅቤ ቀቡት እንዳይነጣ ሌሎች ደግሞ/ ጸጉር ያውጣ/ስለሚባል የአካባቢውን አጠቃቀም ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል ፡፡

2. **አቅርቦት**

መምህር ከላይ ባዜሙት ግጥም ውስጥ የሉትን ፊደላት ዘሮች እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

ለምሳሌ፡-

በ በሉ

ቡ ቡሄ

መ መጣ




ሁ ሁሉ

ያሉትን ቃላት እንዲነጣጥሉ ያድርጉ፡፡

በመቀጠል በ፣ሰ፣ሸ፣ከ፣ፊደላትን ዘሮች በተማሩት መሠረት እንዲጠሩ እያደረጉ ከዚያም ቃላቱን እንዲመሰርቱ ሥዕሉን ያሳዩአቸው፡፡

**መልመጃ**

ሥዕሉን በማየት ቃላት እንዲመሰርቱ ያግዟቸው ፡፡


*ግምገማ*

በዚህ ምራፍ የቀረቡትን ተግባራት በክፍልና ከክፍል ውጪ በግልና በጥንድ እንዲተገብሩ ክትትል በማድረግ ግብረ መልስ መስጠት ይገባል፡፡ ሥዕሉን በመመልከት እንስሳትን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡ሆሄያትን ደጋግመው በማንበብ በደብተራቸው እንዲጽፉ ያግዟቸው የጻፉትንም ክትትል በማድረግ ግብረ መልስ ይስጧቸው፡፥በአጠቃላይ በትምህርቱ አቀራረብ እንደተገለጸው የሚከተሉትን የመገምገሚያ ስልቶች በመጠቀም የተግባር ግምግማ ማድረግ ይቻላል፡፡

- የቃል ጥያቄ
- የጥንድ ስራ
- የክፍል ስራ
- በመምህሩ የሚሰጥ ግብረ መልስ የመሳሰሉትን መጠቀምተገቢ ነው፡፡

## በመጨረሻም

በምእራፍ የቀረቡትን ዓላማዎች በማስታወስ በምእራፉ የቀረቡት ዓላማዎች በተገቢው መንገድ መሳካታቸውን ያረጋግጡ፡፡

## የማበልጸጊያ ተግባራት

መምህር/ት በማበልጸጊያ ተግባራት የቀረቡት መልመጃዎች የምእራፉን ትምህረት ያቀፉ ናቸው፡፡ የመልመጃዎቹ ዓላማ ተማሪዎች እስካሁን የተማሩትን መሠረት አድርገው እራሳቸውን ችለው በመስራት የራሳቸው ግንዛቤ እውቀትና ክህሎት እንዲፈትሹና የራሳቸውን ከቋንቋው ክህሎት ጋር እንዲያዋህዱ ማድረግ ነው ፡፡ስለሆነም ተማሪዎቹ መልመጃዎቹን ሲሰሩም ሆነ ተግባሩን ሲያከናውኑ ከፍተኛ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ከተቻለም በየእለቱ

ርእሰ ጉዳይ ስለተማሩት ነገር ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የእርስዎ ክትትል ከፍተኛ መሆን አለበት፡፡

## መርጃ መሳሪያ

በክፍለ ትምህርቱ የቀረቡት ይዘቶች የቤት እንስሳ ድምጾች በመሆናቸው ክፍል ውስጥ ይዞ መግባት ስለሚከብድ በሥዕል መልክ ማቅረብ ይመረጣል፡፡ስለሆነም ድምጻቸውን በስልክ በመጫን ማሰማትና ተማሪዎችም እንስሳቱን በቅርበት ሊያውቋቸው  ስለሚችሉ በማስመሰል እንዲያሰሙ ማድረግ ይቻላል፡፡

- በመናገር ተግባር የእንስሳቱን ሥዕል እየተመለከቱ ይህ በግ ፣በሬ፣ ፍየል፣ፈረስ  ነው እያሉ የእንስሳቱን ሁኔታ እንዲገልጹ ማድረግ፡፡
- የንባብ ትምህርቱን ለማስተማር ባለሁለት እግር ፊደላትን እንዲያነቡ ሲያነቡም በመዝሙርና በዘፈን መልክ መሆን አለበት፡፡ይህም ደጋግመው በጨዋታ መልክ እንዲለምዱት አስተዋጽኦው የጎላ ነው፡፡እርስዎም በደንብ መከታተል ይኖርብዎታል፡፡
- የቀረቡት ሆሄያት ለማስተማር አጋዥ የሆኑ ስእሎችን የቤት ቡችላ፣ ቢላዋ፣ቦርሳ፣ውሻ፣ድመት፣በግ፣ከበሮ፣ማሲንቆ፣ክራር፣ዋሽንት፣ጥሩምባ የመሳሰሉትን  በማሳየት ማምጣት የሚቻለውን በማምጣት ያሳዩዋቸውና መማር ማስተማሩን ተጨባጭ ያድርጉት፡፡

# አስራ አንደኛ ክፍለ ትምህርት

# የምእራፍ ማጠቃለያ

## ማነቃቂያ

መምህር በክፍለ ትምህርት አንድ በሥዕል የተገለጹትን እንስሳትና የሙዚቃ መሳሪያዎች ድምጽ አሰሟቸው፡፡

## አቅርቦት

መምህር ተማሪዎች እንደማነቃቂያ ያሰሟቸውን የእንስሳትና የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ድምጾችን ስማቸውን እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎቹ በት/ቤት ካሉ በማሳየት ከምን እንደተሰሩ ይጠይቋቸው፡፡ ለተወሰኑ ተማሪዎች በጋራ እንዲመልሱ እድሉን ይስጡ፡፡

በመቀጠል የውሻ፣ድመት፣የበግ ከቤት እንስሳት እንዲሁም የከበሮን የማሲንቆን፣ክራር፣ዋሽትና ጥሩምባ በአካባቢው በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉትን በማሳየትና በማሰማት እንዲያስታውሱ ያድርጉ፡፡

በተጨማሪም የቤት ውስጥ ቁሶችንም ስምና አገልግሎት ይንገሯቸው፡፡ እነሱም ሲኒ፣ጀበና፣ሙቀጫ ፣ዘነዘና፣ምጣድና ሳህን የተወሰኑት እንደሆኑ በመንገር ሌሎች የቤት ውስጥ ቁሶችን ስም እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

የልብስ ዓይነቶችንም ተማሪዎችን እያሥነሱ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡በዚሁ ተማሪዎቹ ወጥተው የለበሱትን ሲያሳዩ የሚሰጣቸውን ተግባር እየተወጡ እንደሆነ ይንገሯቸው፡፡

በመጨረሻም ስለእንስሳ ድምጾች ስለቁሳቁስና ስለልብስ ኣይነቶች እንዲያውቁ በሚያገኙት አጋጣሚ ሁሉ እንዲለዩ ይንገሯቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት አስራ ሁለት

ዓላማ ባለሁለት እግር ሆሄያትንና ቃላትን መከለስ

1. **ማነቃቂያ** ተግባር በተማሪው መጽሐፍ የቀረበውን በ፣ሰ፣ሸ፣ፊደላት በተማሩት መሠረት ደጋግመው እንዲዘምሩ በማድረግ ያስታውሱ በቀላሉ እንዲረዱት ይደግፏቸው፡፡
2. **አቅርቦት**

   መምህር በዚህ ክፍል በተማሪው መጽሐፍ በአቅርቦት ስር የቀረቡትን ሆሄያት በመጀመሪያ እርስዎ መነሻ ፊደሉን በመጥራት ተማሪዎቹ ቃላቱን እንዲመሰርቱና ከቁሱ ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡

   ለምሳሌ፡- በ፣ የበሬ ሥዕልና በሬ ከሚለው ቃል ጋር

   ሸሚዝ፣ሱሪ የመሳሰሉትን በምሳሌው መሠረት ያሰሯቸው፡፡ የቃላት እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ መመሪያ ይስጧቸው፡፡በመጨረሻም ምእራፍ አንድን እንዳጠቃለሉና በምእራፍ ሁለት ጨዋታ የሚል ርእስ እንደሚጀመምሩ ይንገሯቸው፡፡
3. የማበልጸጊያ ተግባራት
4. መምህር/ት የማበልጸጊያ ተግባራቱን ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ በግላቸውና በቤተሰብ ድጋፍ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎም በቤታቸውና በአካባቢያቸው ሚገኙትን ቁሳቁሶች በመጠቀም ሆሄያቱን ይቅረጿቸው፡፡ በመጨረሻ በሆሄያቱ ዘሮች የሚጀምሩትን ቃላት ከቁሶቹ ጋር በማገናዘብ እንዲያነቡና እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

**መርጃ መሳሪያዎች**

ቁሶቹንና እንስሳቱን የሚገልጹ ስእሎች ፣የፊደል ገበታ፣ፎቶዎች

**ግምገማ፡-**

ሆሄያቱን በትክክል እንዲጠሩና እንዲገልጿቸው እንዲጽፉ ያድርጉ በፊደላቱ የሚጀምሩ ቃላትን ከሥዕሉ ጋር ያዛምዱ፡፡ያዛመዱትን ሥዕል ስያሜ ይጻፉ የማዳመጥ ፣የማንበብ፣የመጻፍ፣መልመጃዎችን ያሰሯቸው፡፡

በመጨረሻም እንቆቅልሽ ይጠይቋቸው፡፡

ጠያቂ መምህር                    መላሽ ተማሪ

ስትሰጥ እንደ እናት ስትነድፍ እንደ እንጀራ እናት ንብ

# ምእራፍ ሁለት

# ምዕራፍ ሁለት ፊደል በጨዋታ

## ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፡-

- **ፊደላትን (ሆሄያትን) በመዝሙር መልክ ያነባሉ፡፡**
- **በመዝሙር መልክ የሚሰሙ ፊደላትን ከነዝርያቸው ይጽፋሉ፡፡**
- **ከተዘረዘሩ ፊደላት ቃላትን ይመሰርታሉ፡፡**

## ክፍለ ትምህርት አንድ

አላማ ማዳመጥ

1. ማነቃቅያ ተግባራት ፡-

በስልክ የተጫኑ መዝሙሮችን ያሰሟቸው

ወንድሜ ያዕቆብ ተኛህ ወይ፣

ደወል ተደወለ ተነሳ ተነሳ-

እሺእነሳለሁ እሺ እነሳለሁ ፣

ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን በልቼ

ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ

መልካም እውቀትን እገበያለሁ፡፡ማሰማት ከመጀመርዎ

በፊት በፊደሎቹ የሚጀምሩ ቃላት ያሰሟቸው  ይህም

ልጆቹን በማነቃቃት የጎላ አጽተዋጾ ያበረክታል፡፡

2. አቅርቦት ፡-

በመማሪያ መጽሐፋቸው የቀረቡትንና በመዝሙር መልክ ያሰሟቸውን መዝሙሮች በደበተራቸው አዲገለብጡ ያድርጉ ሆህያቱንና ቃሉን በትክክል አዲያዛምዱ ይደግፏቸው መስመር ጠብቀው ማጻፋቸውን/ ቃሉንና ሆህያቱን በትክክል መጻፋቸውን ክትትል ያድርጉ ፡፡

2. መልመጃ

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ በማለት የመጀመሪያውን ሆሄ በመስጠት ያደመጡትን ቃል ሲጠሩ በቦርድ ላይ ያስፍሩ ይህም ምን ያህል እዳዳመጡ ለማወቅ ከፍተኛ አስተዋጾ አለው በተቻለ መጠን የሁሉንም ተማሪ ስራ ይከተታሉ ያበረታቱዋቸው ያልገባቸው ነገር ካለ ይጠይቋቸው

## ክፍለት ትምሕርት ሁለት

አላማ በባለ ሁለት እግር ሆሄያት የሚጀምሩ ቃላትን ከሥዕል ጋር ማዛመድ

መግቢያ ፡-

ባለፈው ክፍል ስለምን እንደተማሩ በማስታወስ በሀ= ሃብል በ ለ = ለውዝ በ ሐ= ሐኪም እያሉ ቃላትን እንዲመሰርቱ ያበረታቱ እርስዎም ያስታውሱዋቸው:: የእለቱን ርእስ በሁለት እግር ሆህያት አ ፡ በ ፡ ሰ ፡ ሽ ፡ ከ ሆሄ የሚጀምሩ ቃላትን ከያዙ ሥዕል ጋር ማዛመድ እደሆነ ይንገሩ::

አቅርቦት ፡-

መምህር በመማርያ መጽሐፍ ላይ ያለውን ሥዕል በሚገባ ያሳዩዋቸው በማስተካከል አበባ በምን ፊደል ይጀምራል::

የበግ የመጀመርያው ፊደል በ = የመጨረሻው ግ እያሉ ሁሉንም ፊደላት ከቃላቱና ከሥዕሉ ጋር እዲያዛምዱ ያግዟቸው ድምጾቹንም በደንብ እንዲጠሩ ይርዷቸው::

**መልመጃ**

በየዘራቸው በመለየት ያሳዩዋቸው

1. አ =አበባ
   አየ
   አየር
2. በ= በግ
   በሬ
   *በርጩማ*
3. ሰ = ሰው
4. ሸ= ሸማኔ
5. ከ = ከበሮ በማለት ቃሉንና ሥዕሉን በማዛመድ ያሳዩአቸውና እዲያድርጉ ያበረታቷቸው


## ክፍለትምህርት ሦስት


### አላማ ፡-ስእሎቹን ሊወክሉ የሚችሉ የመጀመርያ ፊደላትን መጻፍ

**ማነቃቂያተግባር** ፡ መምህር እንደ ማነቃቂያ በሰላምታ የቀረቡላቸውን ላባ ፡ ኤሊ ፡ አልጋ የመሳሰሉት በምን ከምን እደሚገኙ ይጠይቋቸው እኔ የለበስኩት ምንድነው? ሰው ሲደክመው ምን ላይ ይተኛል? ብለው ይጠይቋቸው


**አቅርቦት ፡-**መምህር ላ ፡ ል ፡ ኩ ፡ አ፡ ኤ ፊደላት ጥቁት ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያንብቡላቸው ዘሮቻቸውንም ይንገሯቸው በመቀጠል ሥዕሉን ያሳዩዋቸው

ል ልብስ



ላ=አ= 

ኩ = 

ኤ 

እያሉ እዲያዛምዱ ያድርጉ በመቀጠል ስራቸውን ይመልከቱ እዲበረታቱ ያድረጋቸው

3. **መልመጃ**

ቀጥሎ በቀረቡት ሆያት የሚጀምሩትን ቃላት መጻፍ

**ሥዕል**

ላ ፡- ላባ

ል ፡- ልብስ

ኩ ፡- ኩባያ

አ፡- አልጋ

ኤ ፡- አሊ እያሉ ቦርድ ላይ እዲጽፉ ያድርጉ።

**ክፍለ ትምህርት አራት ፡-መናገር**

አላማ ፡-ባለ ሁለት እግር ፊደላትን ማንበብ እና መጻፍ

1. መግቢያ

መምህሩ ትምህርት በማነቃቅያ ክፍል በ ቅረጫት ቀርበዋል ወይም ተማሪዎቹ አ . በ . ሰ ሽ. ከ . ለ ፊደላጽነ ዘሮችን በቅደም ተከተል እዲናገሩ ያድርጉ ተግበሩ ግልጽ እዲሆንላቸው መጻፉቸው ላይ ያለውን ይመልከቱ

ምሳሌ ፡- ለሉ ሊ ላ ሌ ል ሎ

2. **አቅርቦት**

በዚህ ክፍል በተማሪ መጻህፍት የቀረቡትን ሆሄያት ከነ ዘሮቻቸው ቀርበዋል ደጋግመው ያንኑናቸው። እያነበቡ ፡ በደበተራቸው ይጻፉ ፡ እሱ ይመራቸዋል ፡ እደጹፍ ያገዛቸዋል ። በመቀጠል በሆህያቱ ቃላት ይመሥርቱ።

ለምሳሌ ፡-አ፡ አበባ ኡ፡ ኡመር ፡ ኢ ፡ኢሳያስ   አ ፡ አውድማ   ኤ ፡ ኤልያስ ፧ ኦ ፡ ኦሞ እያሉ እዲለማመዱ ያድርጎ ።

3. **መልመጃዎች**

4. በመልመጃው ተማሪዎች በሆሄዎች በመጀመርያ ዘር የተጻፉትን በማንበብ እና በጽሑፍ አቅርቦት ላይ ባለው ምሳሌ መሠረት ተግባራቸውን እዲያዳብሩት ያገዟቸው፤ ያለማምዷቸው፡፡ እየተዘዋወሩ ይከታተሉ በትክክል መጻፋቸውንም ያረጋግጡ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አምስት

## የቃላት ምሥረታ

1. **መግቢያ**

መምህር በክፍለ ትምህርት አራት የተማሩትን ፊደላት ያስታውሷቸው፡፡ ምን እንደተማሩ ይጠይቁ እና የእለቱን ትምህርት የቃላት ምሥረታ እደሆነ ይንገሯቸውቃላቱበደብተራቸው ደጋግማመው እንዲጽፉ ያድርጓቸው (ፊደላቱ) አ፡ በ ፡ ሰ ፡ ለ ፡ ከ ናቸው፡፡

2. **አቅርቦት**

በዚህ ክፍል በ አ ፡ በ ፤ ሰ ፤ለ ፤ተ ፡-ሆሄያት የተመሰረቱ ቃላት ቀርበዋል በመጀመርያ ቃላቱ በእርስዎ መሪነት እዲያነቡ ከተደረጉ በኋላ በደብተራቸው እዲጽፉ ያድርጉ፡፡

3. **መልመጃዎች**

በመልመጃው ክፍል ተማሪዎች ደጋግመው እዲጽፏቸው በባለ ሁለት እግር ፊደላት የተመሰረቱ ቃላት ቀርበዋል በመጀመርያቃላቱን እርስዎእየመሯቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

በመቀጠል ትዛዙን በተሰጠው ምሳሌ በማስደገፍ ደጋግመው መጻፍ ይለማመዱ፡፡ እርስዎ እየተከታተሉ በትክክል የሆሄያቱን ቅርጽ ያሳዩአቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ስድስት

### ሞክሼ ፊደላት

አላማ ፡- ሞክሼ ፊደላትን ማንበብ

**1. ማነቃቂያ**

በ ዚህ ክፍል የቀረቡትን ምክሴ ፊደላት ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት አ ፤ በ፤ ለ ፡ ከ ፡ ሰ ስም የሚጀምሩ ስም ያለቸውን ተማሪዎች እንዲቆሙ ያድርጉ አበበ ፤አይናለም ፤ ፀሃይ ፤ አመት የመሳሰሉ ካሉ በማሥነሳት ስማቸውን እዲጽፉ ያድርጉ፡፡

**2. አቅርቦት**

የቀረበውን ምሳሌ በእርሱ መሠረት አዲያነቡ ካደረጉ በኋላ በደብተራቸው እዲጽፉበማድረግ ይከተታተሉቸው እርስዎም በጥቁር ሰሌዳ ይጻፉት

**3. መልመጃ**

ፊደላቱን ከነዘሩ እዲጽፉ ያበረታቷቸው ተግባራቱን እየጻፉ ይከታተሉ በየግላቸው እዲሰር በማድረግ የሰሩትን በማየት ማስተካከያ ይስጣቸው ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሰባት

**ርእስ ፡-ሆሔያትን ከቃላት ጋር ማዛመድ**

**1. ማነቃቂያ**

በዚ ክፍል የቃላት ምሥረታ ትምህርት ሲሆን በሰንጠረዡ የቀረቡትን

ፊደላት እዲያነቡ በምሳሌ ያሳዩአቸው    ሰ ሠ

**2. አቅርቦት**

በአቅርቦቱ የቀረቡትን ቃላት አሁንም በእርስዎ መሪነት እዲያነቡ ካደረጉ በኋላ በደብተራቸው እንዲጽፉ  በማዘዝ ይከተታሏቸው፡፡

ሀ        ሀብል

ሁ        ሁለት

ሂ        ሂስ

ሃ        ሃይማኖት

ሄ        ሄደ

ህ        ህጻን

ሆ        ሆድ ናቸው፡፡

2.ተመሳሳይ ፊደላትን በመክበብ አሳዩ ምሳሌ፡-

| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀብል | ሁለት | ሂሳብ | ድሃ | ሄደ | ህዝብ | ሆሳዕና |

**ክፍለ ትምህርት ስምንት**

**አላማ**፡-ሆሄያትን ከቃላት ጋር በማዛመድ መጻፍ

በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ፊደላቱን ከነዞሮቻቸው እዲጽፉ ባለማመዳቸው መሠረት ሥዕሉን ከቃላቱ ከመጀመርያ ሆሄ ጋር በማዛመድ ከሥዕሉ ጋር ያዘምዱ በትክክል መስራታቸውን ይከታተሏቸው

ሥዕል

ምሳሌ፡- ሠ፡- ሠራ

ሡ ፡- ሡስ

ሢ ፡- ሢሳይ

ሣ ፡- ሣር

ሤ ፡- ሤራ

ሥ ፡- ሥዕል

ሦ ፡- ሦስት

## ትምህርት ዘጠኝ

በ” ሀ “ ዘር የተመሰረቱ ቃላትን ማዛመድ

1. **ማነቃቅያ** :-

መምህር /ት በማነቃቅያ ስር በቀረበው ሥዕል የተመለከቱትን እዲናገሩበማድረግ ትምህርቱን ይጀምሩ ።

2. **አቅርቦት**

በመቀጠል በአቅርቦት ስር የቀረቡትን የሀ ዘር ሆህያትን በማነበብ ቃለቱን ጋር ያዛምዱ እዲያነቡና በቃሉ ከተገለጸው ሥዕል ጋር እያዛመዱ እዲያነቡ ያገዟቸው ሥራውን የተማሪውን መጽፍ የቀረበውን ተማሪዎች እዲለማመዱ ያድረጉ በደበተራቸውም ይጻፉ ።

3. **መልመጃ**

በመጨረሻ በደብተራቸው የጻፉትን የመጀመርያ ፊደል እየከበቡሙሉቃሉን እዲጠሩ ያድርጉ

ሥዕል

ለምሳሌ :- ሀ = ሀብል

ሁ= ሁለት

ሂ = ሂሳብ

ሃ = ሃያ

ሄ = ሄደ

ህ = ህጻን

ሆ = ሆድ የመሳሰሉትን ያላምዳቸው

## ክፍል ትምህርት  አስር

በ፤ ነ ፤ ኘ ፊደላትን ከዘሮቻቸወቅ የሚነበብ ከሆሄያቱ ጋር ያዘምዱ

1. **የማነቃቅያ ተግባር**

በ፤ነ፤ኘ ፊደላትን ከነዘሮቻቸው እንዲያነቡ ያድርጉ ዘሮቻቸውን በጥቁር ሰሌዳ ይጻፉላቸው

2. **አቅርቦት**

በተማሪው መጻፍ የቀረቡትን ስእሎች ለተማሪዎች በማሳየት የምን ሥዕል እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

ተማሪዎች ሲመልሱ በጥቁር ሰሌዳ ይጻፉ፡፡ በተማሪዎች እንዲጻፍ ያድርጉ፤ ነብር የሚለውን መጀመርያ ስለ ጠሩ በቦርድ ይጻፉ፡፡ የተጻፈው  ነ ፤ ብ፤ ር የሚል መሆኑን ይንገሯቸው፡፡ የነ ዘሮች ብዙዎቹ ቃላትን ለመመሥረት ይመቻሉ፡፡ በዚህ መሠረት ሁሉንም ያሰሯቸው፡- ኑግ ፣ኑ፣ግ፣ ኒያላ ፣ኒ፡ያ፡ላ ቡና፣ ቡ፡ና መሆኑን በየተራ እየተነሱ እዲያነቡ ያድርጉ፡፡

3. **መልመጃዎች**

በመጀመርያ የነ ዘሮችን ከ ሥዕሉ ጋር በማዛመድ በሰራቸው መሠረት በነ ሆሄ የሚጀምሩ ሥዕሉን በማየት ቃል እዲጽፉ ያድርጉ፡፡

### ትምህርት አስራ አንድ

በ "የ፤ነ፤ጠ" ፊደላት የተመሰረቱትን ቃላት ማንበብ

1. **ማነቃቅያ**

በክፈለ ትምህርት 9 የተማሩቸውን የነ - ኘ ዘሮችን እዲያስታውስ ያድርጉ ቃለቱንም ይጥሩ በቀጠል ገ፤ ፐ፤ የሚጀምሩ መሆኑን የተገለጹ ቃላትን ትናገራላላችሁ

**2.አቅርቦት**

በመቀጠል ባቅረቦት ስረ የቀረበውን ፊደላትን በል ልዩ መን ገንገድ ማስተማርና ፊደላቱ የሚጀምሩ ቃላትን እዲናገሩ ያድረጉ፡፡ በተማሪው መጽሐፍ ወካይ ሥዕል ስለሚገኝ የመጀመርያውን ፊደል በመጻፍ በሥዕሉ ላይ ያለውን ቁስ እዲያነቡ ያለማምዷቸው፡፡

**ትምህርት አስራ ሁለት**

**የቃላት ምሥረታ**

ነ፤ኘ፤ገ፤ ፐ ሆህያት የሚጀጀምሩ ቃላትን መመሥረት

**1. ማነቃቂያ**

ኘ ፤ ነ ፤ ፐ የመጀምሩ ሆህያትን የተመሰረቱ ቃላ ትን ስእሎችን በመመልከት አንብበዋል? በዚህ ክፍል እሱን ያስታውሷቸው፡፡

**2. አ ቅርቦት**

ቀደም ብለው ያነበቧቸውን ከላይ በተጠቀሱት ፊደላት የሚጀምሩ ቃለትን በምሳሌ መሠረት እያዛመዱ ይጻፉ ነ ፡- ነበ ር

ኘ ፡- ዋኘ

ገ ፡- ገረፈ

ፐ ፡- ፐርሰት የመሳሰሉትን ከነዘሮቻቸው ጻፉ

**3. መልመ ጃዎ ች**

በ "ነ ፤ ኘ ፤ ነ ፤ ፐ" ፊደላትን በመጠቀም ቃላት ይመሥርቱ በግል እዲሰሩ ያድርጉ፡፡

ይህንን በተግባር ሲሰሩ እርስዎ በሚገባ ይከተታተላ ቸው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## እራስን ማስተዋዋቅ

## ትምህርት አንድ

1. **ማነቃቂያ**

በመናገር ክፍል  እራስን ማስተዋዋቅ በሚለው ትምህርት ማነቃቅያ እዲሆን የተዘጋጀውን መዝሙር ያስዘምራቸው ከዛም ተማሪዎቹ እርስዎን ተከትለው እረሶን ተከትለው ይዘምሩ።

ዳካ ሰኞ  ተወለደ ፡
ማክሰኞ ተራመደ
እሮብ ትምህርት ቤት ሔደ ፡
ሀሙስ ዩነቨርስቲ ገባ ፡
አርብ  አውሮፕላን አበረረ ፡
ቅዳሜ ሚስት አገባ ፡
እሁድ ልጅ ወለደ
የደካ ታሪክ በጣም ያስደስታል

2. **አቅርቦት**

መምህር / ት/ ሀዋሳን በማስተዋወቅ ተማሪዎቹ የርሶን አካሄድ ተከትለው እራሳቸውን እዲያስተዋውቁ እርስ በርስም ሰላምታ መለዋወጥ ንግግራቸውን ክሎታቸውን  ያዳብሩ።

3. **መልመጃዎች**

መልመጃዎችን ለማሰራት ሁሉንም ትዛዝ አርሶ እየጻፉ በሚረዱበት መንገድ ትእዛዙን ያቅረቡላቸው።

ሀ. ስምሽ ማነው
ለ. የተወለድከው የት ነው
ሐ. እድሜሽ ስንት ነው
መ. ስንተኛ ክፍል ነህ

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ቃለ ምልልስ

### 1. ማነቃቅያ

እራሳቸው ይገለጽላታ እርስዎም እራሶን ሲገልቱጹ ተማሪዎቹም በዚሁ መሠረት እራሳቸውን መግለጽ እዲችሉ በተግባር ግንዛቤ እዲያገኙ ያድርጉ ቀጥሎም ተማሪዎቹ በእርስዎ ሞዴል ርስ በራሳቸው እንዲሚጠያየቁ ይንገራቸው ።

### 2. አቅርቦት

ምምህር ተማሪዎች በምሳሌው መሠረት የሚከተሉትን

ተማሪ1. ስምሽ ማነው

ተማሪ 2. ጠንክር እባላለሁ ያንተስ

ተማሪ1. ኤርቆጩ

ተማሪ2. ኤርቆጨ ያባትህ ስም ማነው

ተማሪ1. ጡምደዶ ያንተስ

ተማሪ2.ብረመካ / የመሳሰሉትን ተግባራት ተማሪዎች እዲያከናውኑ ያድርጓቸው፡፡ በተጨማሪመረ ተማሪዎችን ወደፊት እየጠሩ ይጠይቋቸው፤ አነሱንም እዲመልሱ ያድርጉ፡፡

### 3. መልመጃዎች

መልመጃዎችን ለማሰራት ሁሉንም ትዕዛዛት እርስዎ እያነበቡላቸው በቀላሉ በሚረዱበት መንገድ በምሳሌው መሠረት ያሠሯቸው ።

ሀ. ስምህ /ሽ ማነው? (ይበላል?)

ለ. የተወለድከው /ሽው የት ነው

ሐ. እድሜህ/ሽ ስንት ነው?

መ. ስንተኛ ክፍል ነህ/ሽ?

## ትምህርት ሦስት

### አላማ፡- የቤተሰብ አባላት መግለጫ

### 1. ማነቃቅያ ተግባራት

መምህር ፡-ተማሪዎች በእርስዎ መሪነት የሚከተለውን መዝሙር ይዘምሩ

አባቴ እወድሃለሁ 3x
እናቴ እወድሻለሁ 3x
ወድሜ እወድሃለሁ 3x
እናቴ እወድሻለሁ 3x
አክስቴ እወድሻለሁ 3x

### 2. አቅርቦት

መምህር ስለ ቤተሰብ የቀረበውን ሥዕል በማየት ርስ በርስ እንዲጠያየቁ ያደርጉ፡፡ ስንት ወንድም አለህ/ሽ? እህትስ? አያቶችህ? የት ነው የሚኖሩት? እዲጠያየቁና ርስ በርስ እዲወያዩ ያግዟቸው የቤተሰብ አባላትን በሚመለከት የቀረበውን መግለጫም ያንበቡላቸው ፡፡

### 3. መልመጃዎች

በውይይታቸው መሠረት በተማሪው የሰፈረውን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

በሚሰጡት መልስማስተካከያ ያድርጉና ስለ ቤተሰብ አባላት ቤተሰቦቻቸውን እዲጠይቁ ያድርጉ፡፡

# ትምህርት አራት

## የቃላትና የፊደላት ጨዋታ

### 1. መግቢያ

መምህር የሆህያትን ጨዋታ ለማከናወን መጀመርያ የሆህያቱን ዘሮች በጥቁር ሰሌዳ ይጻፉና ይጥሯቸው፡፡

### 2. አቅርቦት

መምህር ሆህያቱን በቦርድ ላ በመጻፍ በተማሪው መጻፍ ላይ የሚታዩትን እናት አባት ወንድም እና እህት የሚሉ የቀረቡትን ሥዕሎች እየለያዩ ይህ ምንድነው? እያሉ ይጠይቁ ከፎቶው በማየት አባት እናት ወንድም እህት እያሉ ሲመልሱ በጥቁር ሰሌዳ ይጻፉ እና እዲያዛምዱ ያገዟቸው፡፡

### 3. መልመጃዎች

የሆህያትን መጀመርያ እየጠሩ ቃላቱን እዲናገሩና እዲጽፉ ያድርጉ፡፡

# ትምህርት አምስት

### 1.ማነቃቅያ

መምህር የ‹ሀ› ዘር ፊደላትን ያንበብቡላቸው፤ በጥቁር ሰሌዳ ላይም ይጻፉላቸው፡፡

### 2 .አቅርቦት

መምህር/ት የሚከተሉትን ቃላት እርስዎን እየተከተሉ በመጥራት እዲለማመዱ ያድረጉ፡፡ ቀጥሎ በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያለውን ስእል እዲመለከቱና መጽሐፍ በማየትና እያንዳዱን በመጠቆም ምን እንደሆነ ይወቋቸው ፡፡

### 3.መልመጃ

መምህር ተማሪዎቹን ባነበቡት ፊደላት መሠረት የቀረቡትን ስዕላዊ ቃላቱን መጻፍ እዲገልጹ ያድረጉ፡፡

# ትምህርት ስድስት

## ፊደላትን ማንበብና መጻፍ

**1.የማነቃቂያ ተግባር**

መምህር በስልክ በመጫን አልያም አመቺ በሚሆንልዎ መንገድ የፊደላትን መዝሙር ያሰሚቸው፡፡ ለንባብም ያዘጋጇቸው ፡፡

**2.አቅርቦት**

መምህር የፊደላትን ገበታ ይዘው በመግባት ተማሪዎቹ እርስዎን እየተከተሉ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ባለፉትም ምዕራፎች በተለያየ መንገድ ሆሄያቱን ስላነበቡ እየወጡ በየተራ እዲያነቡ ያድርጉ፡፡

1. **መልመጃ**

ፊደላቱን ወደ ላይና ታች እየጠቆሙ ይጠይቋቸው፡፡ ማስተካከያም ይሰጣቸው፡፡ ባለፉት ይዘቶች በተቆራረጠ መንገድ ስለተማሩት መለየት ይጠበቅባቸዋል ፡፡

## ሰባተኛ ትምህርት

## አጭር ቃላትን መፃፍ

**1.ማነቃቅያ ተግባር**

መምህር ባለፈው ትምህርት በፊደላትን በማንበብ ጽፈዋል ተግባሩ በቤትም መከናወኑን ያለበት በመሆኑ እንደማነቃቂያ የተወሰኑ ፊደላትን ይጠይቋቸው፤ እርስዎም ይንገሯቸው፡፡

**2.አቅርቦት**

መምህር በተማሪው መጽሐፍ ያሉትንጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸውና ያንብቡት፤ ያነበቡትንም እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ ተግባራቸውንም በደንብ ይከታተሉዋቸው፡፡

**3.መልመጃ**

መምህር በሳጥን ውስጥ ያሉትን ሆህያት በማቀናጀት ቀላል ቃላትን እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡

ምሳሌ ፡- ደጋግመው ያሳዩዋቸው

ምሳሌ ፡- ለቀመ

ገለበጠ የመሳሰሉትን በሁለተኛው መልመጃ

ሀ፡- ሀብት

ለ፡-እህል

መ፡-ሐኪም

ሰ ፡- ክብ

ረ ፡-ጎማ

ሸ ፡-ጣሳ

በማለት እዲያስተካክሉ ይንገሯቸው

## ትምህርት ስምንት

የጎደለውን ፊደል ይሙሉ

**1. ማነቃቂያ**

መምህር ባለፈው ክፍል ስለተማሩት ትምህርት ይጠይቋቸው፤  የጎደሉ ፊደላትን በማሟላት የቃላት ጨዋታ እንዲከናወን ያድርጉ፡፡

### 2. አቅርቦት

በተማሪው መጽሐፍ የቀረበውን ሰንጠረዥ በቦርድ ላይ ይጻፉ በሰጠረዥ ውስጥ መገለጽ ያለባቸውን ቃላት በቀለ፣ ቀሰቀሰ፣ አቀለለ የመሳሰሉትን እዲያሚሉ ያድርጉ በጨዋታ መልክ ቃላት እዲመሰርቱ ይረዷቸዋል፡፡

### 3. መልመጃዎች

በሆህያቱ ቃላት እንዲመሰርቱ የተወሰኑ ምስሎችን በመስራት ያሳያዩአቸው ለምሳሌ ሱሪ፣ጸሃይ ፣ ሀብል ፣ቀሚስ ፣መሐረብ ቀጥሎ የቀረቡትን ሳጥን ውስጥ የጎደለውን የሆሄያት ዘሮችን እደሚያሚሉ ያግዟቸው ፡፡

## ትምህርት ዘጠኝ

ወንዶ እና ሴቴ ጾታን መግለጽ፡፡

### 1. መግቢያ

መምህር በመጀመርያ ወንድና ሴት ተማሪዎችን በማቆም ተግባር ስጧቸው፤ አየለ ምን እያደረገ ወይም እየተደረገ ነው? በማለት ይጠይቋቸው እሷ እሱ እያሉ እዲጀምሩ ያድርጉ፡፡

### 2. አቅርቦት

ትምህርቱን በማቅረብ በመጀመሪያ በተማሪ መጽሐፍ የቀረበውን ሥዕል እደሚመለከቱ ያደርጉ፤ ሥዕሉንም በደንብ ከተመለከቱ በኂላ

1. ይህ -----------------ነው፡፡ 2 . ይህች --------ነች

እሱ ------------እያረገ ነው፡፡ እሷ -----------------እያረገች ነው

### 3. መልመጃዎች

ተግባራቱን በትክክል ለወንድ እሱ፣ ለሴት እሷ፤ ለቅርብ ይህ፣ ይህች በማለት መመለሳችሁን ያረጋግጡ፡፡

## ትምህርት አስር

ሥዕልን በማየት ተግባሩን መግለጽ፡-

### 1. ማነቃቂያ

መምህር ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም በዚህ ክፍል የቀረቡ ተግባራት እዲከናወኑ ያድርጉ፡፡

### 2. አቅርቦት

በመጀመርያ በመማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን ሥዕል በደንብ እዲመለከቱ ያደርጉ በመቀጠልም ምን እያከናወኑ እንደሆነ ይጠይቁዋቸው ፡፡

### 3. መልመጃዎች

በመጀመርያ ሥዕሎችን ደጋግመው ይመልከቱ በመቀጠልም ምን እየተከናወነ እንደሆነ ይጠይቋቸው፤ በጥቁር ሰሌዳም ይጻፉ፡፡ ሁሉም ተማሪ በትክክል መግለጹን ያረጋግጡ፡፡

**ማበልጸጊያ**

የቀረቡት ቃላቱን እዲጽፉና በሆሄያቱ ደግመው ቃላት እንዲመሰርቱ ደግም ቃላት እዲመሰርቱ ያበረታቷቸው፡፡ ተግባሩን ለመስራት እርሰዎ ትዕዛዙን በምሳሌ መሠረት ካስረዳቸው በኋላ በየግላቸው እንዲሰሩ በማድረግ የሰሩትን በማየት ማስተካከያ ይስጧቸው ፡፡

**ግምገማ**

የተለያ ሥዕሎችን ተመልክተው ሆህያቱንና ሥዕሎቹ የሚገልጽ ቃላትን እዲናገሩ የቃል ጥያቄዎችንም እዲመልሱ ማድረግ ቃላትን እዲናገሩ የቃል ጥያቄዎችን እዲመልሱ ማድረግ ይቻላል፡፡ የተማሯቸውን ሆህያት ከነዘራቸው ጥንድ ጥንድ በመሆን እዲያነቡና የቢጤ እርማት እዲያደርጉ በማገዝ መገምገም እስካሁን የተማሯቸውን ሆህያት ከነዘራቸው ጽፈው እንዲመጡ የቤት ስራ በመስጠት፣ በክፍል ውስጥ እዲያቀርቡ በማድረግና በመጨረሻም ማስተካከያ በመስጠት የትምህርቱን ሂደት መፈተሸ ይችላል፡፡ በመጨረሻም የምዕራፍን ትምህርት በማጠቃለል የተለያዩ እንቆቅልሾችን በመስጠት እንዲነቃቁ ማድረግ ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## የእንስሳት ስሞችን አዳምጦ መግለጽ
### ትምህርት አንድ

1. **የማነቃቂያ ተግባር**

በአዳምጦ መረዳት ክፍል ወደቀረበው ትምህርት በቀጥታ

ከመግባትዎ በፊት እርስዎ ቀጥሎ የቀረበውን

"ትምህርት ቤቴ"

ትምህርት ቤቴ፣

ትምህርት ቤቴ፣

የእውቀት መሰረቴ፡፡

እርሳሴን በእጆቼ፣ቦርሳዬን ባንገቴ

ትምህርት ቤት ስሄድ በለጋ ጉልበቴ

ትዝ ትይኛለሽ ዋ!ትምህርት ቤቴ፡፡

የጥናቱ ጊዜ አልፎ ስጫወት ጨዋታ፣

በአልጋ ላይ ስጋደም ጊዜው ሲመሽ ማታ፣

ወይ ትምህርት ቤቴ ትዝታሽ አያልቅም፣

ሳስብሽ እኖራለሁ እስከ ዘላለም፡፡

የሚለውን መዝሙር በመዘመር ተማሪዎቹ እርስዎን ተከትው እንዲዘምሩ በማድግ ያነቃቋቸው፡፡

2. አቅርቦት

መምህር ተግባሩን ለማከናወን ብልጡ ቀበሮ የሚለውን ምንባ አንብቡላቸው፡፡

**ብልጡ ቀበሮ**

አንድ ቀን አንዲት ድመት ከአንድ ነጋዴ  አይብ ሰርቃ ትሄዳለች፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ውሻ ያያታል አይቡን ሊወስድባት ፈለገ ድመት ግን እንቢ ብላ የውሻውን ዓይን መቧጨር ጀመረች፡፡ ውሻው ዳግም መናከስ ያዘ፡፡ ድመት አላዋጣ ሲላት "ቀበሮ ይዳኘን" አለችው፡፡

ውሻውም ተስማማ ቀበሮም ጉዳያቸውን ካዳመጠ በኋላ "የማትረቡ ናችሁ" አለ፡፡ "ቀበሮ የማትረቡ ናችሁ ካለ በኋላ ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል? "

አይቡን በቢላዋ ሁለት ቦታቆርጦ አካፈላቸው ውሻው ግን "የእኔ ድርሻ አንሷል" ብሎ ተቃወመ፡፡ ቀበሮም "አዎ ! እውነትም አንሷል፡፡" በማለት ከድመቷ ድርሻ አንድ ጉርሻ ጎረሰለት፡፡

ድመቷም በተራዋ "እንዴ ! የእኔ ቀንሷል፡፡"እሺ ብሎ ከውሻው ድርሻ ጎረሰለት፡ ፡ በዚህ ሁኔታ ድመትና ውሻ ሲጨቃጨቁ ቀበሮው አይቡን በልቶ ጨረሰው፡፡

በማለት ለምንባብ ያንብቡላቸውና

ከምንባቡ የወጡትን የቀበሮ ፣ የድመት፣ ውሻ ተግባር ምን እንደነበር ለማወቅ

1ቀበሮ ምን አደረገች? ለዳኝነት ተቀመጠች

2.ድመት ምን ሰረቀች? ቅቤ

3.ውሻ ምን አደረገ? ድት ቅቤ ሰርቃ ስትሄድ አየ፡፡

4.ከምንባቡ የተረዱትን ይጠይቁ፡፡

3. መልመጃዎች፡ በመልመጃዎቹ የቀረቡትን ሥዕሎች በምንባቡ ካለው ተግባራቸው ጋር እያዛመዱ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ እርስዎም ያግዟቸው፡፡

## ትምህርት ሁለት

### በሥዕሉ የቀረቡትን ቁሶች ምንነት መናገር

1. የማነቃቂያ ተግባር፡-

ሥዕሎቹን ተመልክተው የተረዱትን እንዲናገሩ ያድርጉመምህር/ት የትህርቱን አቅርቦት በተመለከተ በመጽሐፍ የቀረቡት ሥዕሎች ተመልክተው ምን አገልግሎት እንደሚሰጡ ይጠይቋቸው፡፡ እርስበርስም እንዲነጋገሩ ያድርጉ፡፡ ትዕዛዙን ግልጽ ለማድረግ በመጀመሪያ የሚገኘውን ሥዕል መንገር/ ለምሳሌ ጠመኔ፡- በጥቁር ሰሌዳ ላይ ለመጻፍ ያገለግላል፡፡
በመቀጠል ተማሪዎች በየተራ እየተነሱ የእያንዳንዱን አገልግሎት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

2. **መልመጃዎች**

በመጀመሪያ ተማሪዎች በጥንድ በመሆን ከተወያዩ በኋላ የቁሶቹን ጥቅም ይናገሩ፡፡ እርስዎም እያንዳንዱን ቡድን በማሥነሳት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

## ትምህርት ሶስት

### የቁሶቹን ጥቅም መግለጽ

1. **ማነቃቂያ፡-**

መምህር/ት መምህር ተማሪዎች ሊያነቃቃቸው የሚችል ተግባር ለእርስዎ አመቺ በሆነ መንገድ አሰሯቸው

2. **አቅርቦት ፡-**

በአቅርቦት ክፍል ቀጥሎ የቀረቡትን ስእሎች ደጋግመው ስማቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎቹ በሥዕሉ የተመለከቱትን ነገር እንዲናገሩ ይርዷቸው ፡፡
በማስከተል ለምን አገልግሎት እንደሚዉሉ ይጠይቋቸው ተማሪዎቹ እንዲመልሱ ያበረታቱ፡፡

**3. መልመጃ፡-**

መምህር ተማሪዎች ሥዕሉን በሚገባ ከተመለከቱ በኋላ ሥዕሉን ሊወክሉ የሚችሉ ቃላት ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡ መምህር ሥራውን በምሳሌ ያሳዩዋቸው፡፡

## ትምህርት አራት፡

## የእንስሳ ስሞችን መጻፍ

**1. የማነቃቂያ ተግባር፡**

መምህር ተማሪዎችን በማነቃቃት ወደ ትምህርቱ ለማስገባት የሚያስችሉ መዝሙር ቀርቧል፡፡

ውርዬ ውርዬ አቤት ደስ ስትል፡

እየተጫወተች ወዲያ ወዲህ ስትል፣
ሚያው ሚው እያለች ስትሮጥ፣
የአይጥ ዘሮች ሁሉ ይላሉ ድንግጥግጥ፡፡ የሚለውን እርስዎን
በመከተል ይላሉ፡፡

**2. አቅርቦት፡-**

በተማሪው መጽሐፍ የቀረቡትን ሥዕሎች ያስረዷቸው ቀጥሎም ሥዕሉን ይግለጹላቸው እርስዎ ሲገልጹ እነሱ ስማቸውን ይጻፉ፡፡

**3. መልመጃዎች፡-**

መምህር/ት በመልመጃ የቀረቡትን የቤት እንስሳት ምስል በተመለከቱት መሠረት በትዕዛዝ አንድ ያለውን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

ምሳሌ፡- ከላም ምን እና ምን እናገኛለን?ወተት

ውሻ ምን አገልግሎት ይሰጣል ?ግቢ ይጠብቃል

ዶሮ ምን ትሰጣለች ?እንቁላል

## ትምህርት አምስት፡

## የእንስሳት ስሞችን መጻፍ

### 1. ማነቃቂያ ተግባር፡

መምህር/ት ከተማሪዎች መካከል በማሥነሳት ባላፈው ስለተማሩት ትምህርት ይጠይቁ ሌላኛው የአንድ እንስሳ ስም ወጥቶ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

### 2. አቅርቦት

በመጀመሪያ በተማሪ መጽሐፍ የቀረቡትን የቤት እንስሳት ስሞች በቦርድ ላይ ይጻፉ፡፡ እርስዎን በመከተል እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡

### 3. መልመጃ

በመልመጃ አንድ የቀረቡትን ትዕዛዛት ተማሪዎች እንዲተገብሩያድርጉ፡፡ ከላይ በተማሩት መሠረት በተራ እየተነሱ በጥቁር ሰሌዳ ይጻፉ ስህተት ካለ ተማሪዎች እንዲያርሙ ይርዷቸው፡፡ በመቀጠል እርስዎ ያርሟቸው፡፡

## ትምህርት ስድስት

## የቁሳቁስን አገልግሎት መግለጽ

1. **ማነቃቂያ ተግባር**

   "ትምህርት ቤቴ"

   ትምህርት ተቤቴ፣

   ትምህርት ቤቴ

   የዕውቀት መሰረቴ፡፡

   እርሳሴን በዕጆቼ፣ ቦርሳዬን ባንገቴ

   ትምህርት ቤት ስሄድ በለጋ ጉልበቴ

   ትዝ ትይኛለሽ ዋ! ትምህርት ቤቴ

   በጥናቱ ጊዜ አልፎ አልፎ ስጫወት ጫወታ፣

   በአልጋ ላይስጋደም ጊዜው ሲመሽ ማታ

   ወይ ትምህርት ቤቴ ትዝታው አያልቅም፣

   ሳስብሽ እኖራለሁ እስከዘለአለም፡፡

2. **አቅርቦት፡**

በመማሪያ መጽሐፍ የቀረበው የትምህርት ቁሳቁስ እንዲመለከቱና ስማቸውን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎም ቁሳቁሶቹን በማሳየት የጻፉት ትክክል መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

3. **መልመጃ**

የቀረበውን በአቅርቦት በሥዕል በማየት የጻፉትን እርስዎም ቁሶቹን በአካል ባሳዩዋቸው መሠረት አገልግሎታቸውን በአጭሩ እንዲጽፉ

ያድርጉ

ለምሳሌ ብዕር ፡- ለመጻፍ

ቦርሳ ፡- ደብተር ለመያዝ

እርሳስ፡-ለመጻፍ

ጠረጴዛ፡-ለማስደገፍ

ጥቁር ሰሌዳ፡-ለማስተማሪያ

ማስመሪያ ፡-ለማስመር

ዳስተር፡-ለማጥፋት

ላፒስ፡- ለማጥፋት

መጽሐፍ፡- ለማንበብ

**መልመጃዎች**

ከዚህ በማስከተል ቀደም ብሎ ባነበቡላቸው ተረት ውስጥ የሰሙትን መሠረት በማድረግ ጥያቄዎችን በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ

ለምሳሌ፡ ተኩላና መንገደኛ የት ተገናኙ፡ በመንገድ ለፍርድ ጦጢት ጋ እንሂድ ያለው ማን ነው?

ሰውየው በድርጊት አሳየኝ ብሎ ሰውየውን የጠየቀው ማነው? ጦጢት

## ትምህርት ስምንት

## ማገናዘብ

### 1. የማነቃቂያ

ተግባር መምህር በተማሪ መጽሐፍ የቀረበውን ሥዕል በማየት ይናገሩ

ቦታው የት ነው?



### 2. አቅርቦት

መምህር በተማሪው መጽሐፍ የቀረበውን ምንባብ ያንብቡላቸውና ተማሪዎች በታሪኩ ዋና ገጸ ባህርያት እነማን እንደሆኑ እንዲረዱ ምንባቡን ቆም እያደረጉ ማን ምን አደረገ እያላችሁ ጠይቋቸው፡፡ የማገናዘብ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ያድርጉ፡፡

### 3. መልመጃዎች፡

ከላይ ተረቱን ሲያነቡላው ባመጡት ታሪክ ውስጥ ያሉትን ቦታዎች ይጠይቋቸው፡፡

- መንገደኛው ምን ሆኖ ነበር፡- እርቦት
- መንገደኛው እሰት የት አገኘ  በማሳ
- ሰውየው ምን ነበር ፡ መንገደኛ

## ትምህርት ዘጠኝ

ሆሄያትን ከቃላት ጋር በማጣመር ማንበብ

**ማነቃቂያ**

መምህር እንቆቅልሽ ይንገሯቸው

| ጠያቂ | መላሽ |
| --- | --- |
| እንቆቅልህ /ሽ | ምንአውቅልህ /ሽ |
| 1. ማሳው ነጭ ዘሩ ጥቁር | መጽሐፍ |
| 2. ቆቤን አውልቀው ዘቀዘቁኝ<br>ወገቤን ይዘው ነቀነቁኝ | ብዕር |

3. መልመጃዎች፡

ከላይ የቀረበው ትምህርት ሆሄያቱን በእነርሱ የሚጀምሩ ቃላት ጋር በማዛመድ እንዲያነቡ ያድርጉ በመቀጠል ቃላቱን ያዛምዱ በቃላቱ የተመሰረቱትን ይጻፉ፡፡

## ትምህርት አስር

ትዕዛዛት በማዳመጥ መተግበር

1. **ማነቃቂያ**

ተማሪዎችን ጥቁር ሰሌዳን እንዲያጠፉ በማድረግ ምን እየሰሩ እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡

2. **አቅርቦት**

መምህር ተማሪዎች ሥዕሉቹን እንዲመለከቱ ያድርጉ በመቀጠል ስለ ሥዕሉ ምን እየተደረገ እንደሆነ ይጠቋቸው፡፡

3. **መልመጃዎች**

መምህር ተማሪዎች ሥዕሎቹን እየተመለከቱ እንዲተገብሩ ያድርጉ እየወጡም ይናገሩ በተግባር እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## አካባቢያችን

1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ያነባሉ፡፡
- በማዳመጥ ቃላትን ይለዋወጣሉ
- አዳዲስ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡ (በሚፈጠር አውድ)
- ሆሄያትን በማጣመር ቃላትን ይጽፋሉ፡፡

ቃላትን በተመሳሳይና በተቃራኒ ያዛምዳሉ፡፡

### ትምህርት አንድ

### ትምህርት አንድ በ፤ቀ፤ጠ፤መ፤ረ፤ደ፤ ዘር ፊደላትን በማጣመር ቃላትን ማንበብ

1. **ማነቃቂያ፡**

በመምህር/ት ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም በዚህ ክፍል የቀረቡትን ሆሄያት ዘሮች እንዲያነቡ በማድረግ ያነቃቋቸው፡፡

2. **አቅርቦት፡-**

ተማሪዎች ፊደል የሚጀምር ቃል ያለው ሥዕል ቀርቧል፡፡

ሥዕሉን ከቃሉ ጋር እንዲያዛምዱና የቁሱን ቃል የመጀመሪያ ፊደል በመጥራት እንዲሞሉ ያድርጉ ምሳሌም ያሳዩዋቸው፡፡

ምሳሌ፡- በር፣ቀበቶ፣ቀሚስ፣ቡችላ፣ቁልፍ፣ በግ

3. **መልመጃዎች፡**

በ"ቂ" ቂጣ፤ ቢ፡ ቢላዋ ""ባ"" ባቄላ፣ ቃ፤ ቃሪያ ለሚሉት ቃላት የተሰጡትን የመጀመሪያ ፊደል በማሟላት ከላይ የቀረበውን ቃል እንዲያሟሉ ያግዟቸው፡፡ የጻፉትን ቃል ቂጣ፣ ቢለዋ፣ ባቄላ፣ ቃሪያ፣ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

## ትምህርት ሁለት

ቃላት እያጣመሩ ማንበብ

1. ማነቃቂያ መምህር/ት ተማሪዎቹን ለማነቃቃት ቀጥሎ የቀረቡትን ሆሄያት ያንብቡላቸው

   ቀ፡- ቢ ቀቢ

   በ-ቂ በቂ

   ቅ--ብ ቅብ

   ቆ- ብ ቆብ

   ቆ- ቅ ቆቅ

2. አቅርቦት ፡- በአቅርቦት የቀረቡትን ቃላት አሁንም በእርስዎ መሪነት ሥዕሉን እየተመለከቱ ቃሉን በደብተራቸው በመጻፍ እንዲያነቡ በማዘዝ ይከታተሏቸው፡፡
3. በመልመጃው የቃል መጀመሪያ ሆሄያት በመጠቀም ቃላት እንዲመሰርቱ የመሰረቱት ቃል የትኛውን ቁስ እንደሚገልጽ እርስዎም እርማት ይስጡ፡፡

ጠ = ጠርሙስ

መ = መቀስ

ሚ = ሚጡ

ጢ= ሚጢጢ

ሙ = ሙዚቃ

ጦ = ጦጣ

ጫ = ጫማ

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችና የሚሰሩባቸው ቁሳቁስ፡-

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎ የተለያዩ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት በዓይነት ተከፋፍለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በስንት አይነት ይከፈላሉ፡፡

የኢትዮጵያ የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች በሶስት አይነት ሊከፈሉ ይችላሉ እነዚህም የክር፣ የትንፋሽና የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ይባላሉ፡፡ የክር የሚባሉት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ክራር፣ ማሲንቆ፣ በገና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት ደግሞጥሩንባ ፣ ዋሽንት፣ እምቢልታና የመሳሰሉት ሲሆኑ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ደግሞ ከበሮ፣ ነጋሪት፣ ጽናጽል፣ ደውል፣ ቃጭልና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እነዚህ ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች ባላዊ በመሆናቸው አካባቢያዊ ከሆኑ ቁሳቁሶች ይዘጋጃሉ፡፡ በዚህ መሠረት የክር የሚባሉት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአብዛኛው ከጅማትና ከእንጨት ውጤቶች እንዲሁም ከቅልና መሰል ቁሳቁሶች ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡

የትንፋሽ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአብዛኛው ከቀርከሀ፣ ወይም ከሸምበቆ ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህም በተጨማሪ ቅልና ሹል ብረት ለሥራው ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

የምት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከተለያዩ ቁሶች ይዘጋጃሉ እነዚህም እንጨት፣ የከብት ቆዳ፣ ጠፍር፣ ብረት፣ መዳብ፣ ነሀስ፣ እንዲሁም ድቡልቡል ብረቶች ሊሆኑ ይችላሉሉ፡፡

## ትምህርት ሶስት

አውድ በመፍጠር ቃላትን መመሥረት

1. **ማነቃቂያ፡-**

ስለሚያውቋቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች ይጠይቋቸው፡፡ ድምጽ ያሰሟቸው፣ ዋሽንት ከበሮ

2. **አቅርቦት፡-**

የሙዚቃ መሳሪያዎች ምንባቡን ያንብቡላቸው ቆም እያደረጉ በስንት እንደሚከፈሉ ይጠይቋቸው

ምንባብ

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

ከምንባቡ ምን ተረዳችሁ በማለት የግንዛቤ ጥያቄቆችን ይጠይቋቸው

3. መልመጃዎች፡-

በቁጥር 1 የቀረበውን ጥያቄ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በሶስት እንደሚከፈሉ እነርሱም የክር፣ የትንፋሽ፣ የምት እንደሆኑ ከምንባቡ ተረድተዋል፡፡

በተራ ቁጥር ሁለት የቀረበውን ስለትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንዲናገሩ ያድርጉ እነርሱም ጡሩንባ፣ ዋሽንት፣ እምቢልታና ሌሎችም ናቸው፡፡

ከቀርከሀ የሚሰሩ የትንፋሽ ባህላዊ መሳሪያዎችን እንደሆኑ ይንገሯቸው፡፡

## ትምህርት አራት

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ከስማቸው ጋር ማዛመድ፡፡

1. **ማነቃቂያ፡-**

የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ተናገሩ፡፡ ከእነርሱ መካከል በተለምዶ ዋሽንት በስፋት የሚጠቀመው እረኛ ነው፡፡

2. **አቅርቦት፡-**

መምህር በመጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ በሥዕል የቀረቡትን የሙዚቃ መሳሪያዎች ምን እንደሚባል ይጠይቋቸው በመቀጠል ሥዕሉን ከቃሉ ጋር እንዲያዛምዱ ይዘዟቸው ትክክለኛውን የሙዚቃ መሳሪያ እስከነስያሜው ማዛመዳቸውን ያረጋግጡ፡፡

3. **መልጃዎች፡-**

በተራ ቁጥር አንድ በቀረበው ጥያቄ ጥሩንባ ከምን ይሰራል የሚል ነው፡፡ ከመዳብ (ከነሀስ)፣ ከቀንድ ወዘተ የጥሩምባ ድምጽ እንዲያሰሙ ያድርጉ፡፡

ዋሽንት ከምን ይሰራል? ከሸንበቆ፣ ከብረት በማለት መመለሳቸውን ያረጋግጡ

## ትምህርት አምስት

የሙዚቃ መሳሪያዎችን ስም መናገር

1. **ማነቃቂያ፡-**

መምህር/ት ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ድምጽ እንዲያሰሙ በማድረግ ያነቃቋው፡፡ በማስመሰልም ማዜም ይቻላል፡፡

2. **አቅርቦት፡-**

መምህር/ት ተማሪዎች በሥዕሉ የሚመለከቱትን የሙዚቃ መሳሪያዎች ለጓደኞቻቸው እንዲነግሩ ያድርጉ በመቀጠልም እንዴት ድምጽ እንደሚሰጡ ይጠይቋቸውና በተግባር በማሳየት ያግዟቸው ለምሳሌ ክራር፣ እጅን በመጠቀም ዋሽንት በትንፋሽ በማለት ያሳዩዋቸው፡፡

መምህር/ት የሙዚቃ መሳሪያዎቹ እንዴት ድምጽ እንደሚሰጡ ያሳዩዋቸው ፡፡

ለምሳሌ፡ ነጋሪት በመጎሰም (በምታት)

ደወል በመደወል (ይደወላል) እና በመሳሰሉት መንገድ ሙከራዎቹ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## ትምህርት ስድስት

### የ "ጠ" ሆሄያት ዘሮች ቃላትን መመሥረት

1. **ማነቃቂያ፡-**

መምህር፡- የ ''ጠ'' ዘር ሆሄያትን በቦርድ (በጥቁር ሰሌዳ) ይጻፉላቸውና ያስታውሱ

2. **አቅርቦት፡-**

መምህር/ት በሆሄያቱ ቃለት እንዲመሰርቱ ያግዟቸው፡፡

ቃላቱ ፡ ጠ= ጠረጴዛ ጣ= ጣት

ጡ = ጡት ጤ= ጤፍ

ጢ = ጢስ ጥ= ጥጥ

ጦ = ጦር (ጦጣ)

**መልመጃዎች**

መምህር በ "ጠ" ዘር የመሰረቱትን ሆሄያት ለጓደኞቻቸው ባነበቡት መሠረት በትክክል መጻፋቸውን ያረጋግጡ፡፡

## ትምህርት ሰባት

ሆሄያቱን ከነዘሮቻቸው ማንበብ

1. ማነቃቂያ፡ መምህር ተማሪዎች "ሐ" "ጨ" ዘር ፊደላትን ያንብቡላቸውና ቦርድ ላይ ይጻፉ በሆሄያቱ የሚጀምሩ ቃላትን ይናገሩ

   ጨረቃ

   ሐብል

2. አቅርቦት በዚህ ክፍል ሆሄያቱ ከነዘሮቻቸው ቀርበዋል ሆሄያቱን እንዲያነቡ ያድርጉና በሆሄያቱ ቃላትን ይመሥርቱ የመሰረቱትን ቃላት ለጓደኞቻቸው ይናገሩ፡፡
3. መልመጃዎች ፡- በመልመጃው ክፍል ተማሪዎች ደጋግመው ከላይ የተናገሩዋቸውን ቃላት ከነዘሮቻቸው ቀርበዋል ለቃላቱ መነሻ የሚሆኑ ሆሄያትን የያዙትን ቃላት አዛምዱ፡፡

   1. ጣ ጣሳ
   2. ጨ ጨው
   3. ሐ ሐመር
   4. ጮ ጮጮ
   5. ሒ ሒሳብ
   6. ጠ ጠርሙስ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡ ቃላቱንም እንዲዋቀሩ ይከታተሉ፡፡

## ትምህርት ስምንት

በሆሄያቱ የተመሰረቱ ቃላትን መጻፍ

**1. ማነቃቂያ፡-**

በዚህ ክፍል የቀረበውን የቃላት ምሥረታ ትምህርት ሲሆን በመጀመሪያ በሰንጠረዥ የቀረቡትን ሆሄያት አግድምና ቁልቁል በመገጣጠም ቃላት እንዲመሰርቱ እርስዎ ምሳሌ በመስጠት እንዲሞክሩ ያነቃቋቸው፡፡

**2. አቅርቦት፡-**

መምህር/ት ተማሪዎች በአቅርቦት የቀረቡትን ቃላት ሲያነቡ እርስዎ ይከታተሏቸው ቃላቱን በትክክል ማንባቸውን ይከታተሉ የተሳሳተ ካለ ያስተካክሏቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ጮ | ጮ |
| ጮ | ሌ |

3. መልመጃዎች፡-

በመልመጃው የቀረቡትን ምልክቶች በመገጣጠም ከስር የቀረቡትን ሆሄያት ከነዘሮቻቸው መጻፍን ይለማመዱ በመቀጠልም የቀረበውን ምስል ተጠቅመው ምስሎቹን የሚገልጽ ቃላት መስርተው እንዲናገሩ ቃላቱንም በደብተራቸው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

ጭ ጭራ

ጠ ጠጣ

ሐ ሐብል

መርጃ መሳሪያዎች

4. በመማሪያ ክፍል የሚታዩ ጠረጴዛ፣ ጠመኔ፣ እንዲሁም ሚዛን ፡- ሙዝ፣ ጣት፣ ማንኪያ፣ ጢም መሰላልየመሳሰሉት ማቅረብ የሚቻለው በአካል በማምጣት የማይቻለውን ሥዕል በማሳየት ትምህርቱም ተጨባጭ ለማድረግ ያግዛል፡፡
5. የተለያዩ ቁሶችን ሥዕል በማየት ስማቸውን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው በምዕራፍ የቀረቡትን ሆሄያት የተመሰረቱ ሥዕሎችን ተመልክተው ሆሄያትንና ሥዕሉን የሚገልጹ ቃላትን እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ ግምገማውን ማካሄድ ይቻላል፡፡ ሆሄያቱ ከነዘሮቻቸው በማንበብ የቢጤ እርማት እንዲያደርጉ በማድረግ መገምገም የቤት ስራ በመስጠት ማስተካከል ይቻላል፡፡ የተሰጡትን ሙከራዎች በየትምህርቱ ርዕስ በምሳሌ ስለቀረበ ይጠቀሙ፡፡

# ትምህርት ዘጠኝ

አዳምጦ መጻፍ

1. **ማነቃቂያ፡**

ተማሪዎች ወደ ትምህርቱ ለማስገባት የት ተወለዳችሁ? -------------
--የሚኖሩበትን ዞን ከተማ ---------------- ነው የመሳሰሉትን ይጠይቁ

2. **አቅርቦት ፡**

በተማሪው መጽሐፍ የዞን ስሞች ቀርበዋል፡፡ የዞኑን ከተሞች ስም ሰንጠረዥ በመሳል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይሳሉ፡፡ በግራ በኩል የዞኑን ከተማ ይጻፉ በፊት ለፊት ወይም በስተቀኝ ከተማውን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ በትክክል መጻፋቸውን ይከታተሉ፡፡ በምሳሌ ያሳዩዋቸው፡፡

**ዓላማ ፡- አዳምጦ መናገር**

1. የሚከተሉትን የዞን ዋና ከተሞች መምህራችሁን በማዳመጥ ተናገሩ ጻፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ሀላባ | ቁሊቶ |
| 2 | ሀዲያ | ሆሳዕና |
| 3 | ዳውሮ | ተርጫ |
| 4 | ጉራጌ | ወልቂጤ |
| 5 | ጌዴኦ | ዲላ |
| 6 | ከምባታ | ዱራሜ |
| 7 | ስልጤ | ወራቤ |
| 8 | ጎፋ | ሳውላ |
| 9 | ጋሞ | አርባ ምንጭ |
| 10 | ወላይታ | ሶዶ |
| 11 | ደቡብ ኦሞ | ጂንካ |
| 12 | ኮንሶ | ካራት |
| 13 | ሰገን | ሰገን |

## ትምህርት አስር

፡ ! ፣ ፡፡ ?ሥርዓተ ነጥብ መጠቀም

**1. ማነቃቂያ፡-**

መምህር/ት ለተማሪዎች ሰላምታ ካቀረቡ በኂላ ለተማሪዎች ተነስ ተቀመጥ አይነት ተግባራትን በማሰራት ምን እያደረጉ ነው የሚል ጥያቄ ለተማሪው አቅርቡ፡፡

**2. አቅርቦት፡-**

መምህር በተማሪው መጽሐፍ ለቀረቡት ሥርዓተ ነጥቦች አገልግሎት ለተማሪዎች ማብራሪያ ይስጡ፡፡

ሁለት ነጥብ (፡)፡- ቃልን ከቃል ደቂቃን ከሴኮንድ ለመለየት ይጠቅማል፡፡

ቃለ አጋኖ ማጋነን (!)፡- ትእዛዝን ለማስተላለፍ የረጠቅማል፡፡

ጥያቄ ምልክት (?)፡- ተጠያቂው መልስ እንዲሰጥ

ነጠላ ሰረዝ (፣)፡- አበበ፣ አለሙና ፈይሳ አይነት ተደራራቢ ስሞችን ለመለየት ያገለግላል፡፡

**3. መልመጃዎች፡-**

መምህር/ት በተማሪው መጽሐፍ 1-3 የቀረቡትን ጥያቄዎች ስርዓተ ነጥብ የላቸውም ተማሪዎች በተገቢ ቦታ ተስማሚውን ስርዓተ ነጥብ እንዲጠቀሙ ያድርጉ፡፡

1. ክራር ፣ መሰንቆና በገና የሙዚቃ መሳሪያዎች ናቸው፡፡
2. ከበሮ ለመስራት፡ የዋንዛ እንጨት ይጠረባል፤ የከብት ቆዳ ይፋቃል፡፡
3. ምን አይነት የሙዚቃ መሳሪያ ትወዳላችሁ? የመሳሰሉትን በትክክል ማስገባታቸውን ያረጋግጡ፡፡
4. ጉራጌ፣ከምባጽ፣ጌዴዴኦ፣ጎፋና ባስኬቶ በደቡብ ክልል የሚገኙ ዞኖች ናቸው፡፡

   ከክራር------ይመታል፣ይደረደራል፣ይቃኛል

   ዋሽት------ይነፋል

   ደወል------ይደወላል

   መሰንቆ----- ይገዘገዛል (ይመታል

   ነጋሪት------ይጎሰማል

## ምእራፍ ስድስት

### ንጽህና አጠባበቅ

1. **ሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኂላ ተማሪዎቹ፡-

- የግል ንጽህና አተባበቅን ይረዳሉ/ይተገብራሉ
- ስለግል ንጽህና አጠባበቅ ምንባብ አዳምጠው ለጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ
- ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የወጡ አዳዲስ ቃላትን ታነባላችሁ
- ንጽህናን ካለመጠበቅ የሚመጡ ጉዳቶችን ይናገራሉ
- አዳዲስ ቃላትን ያነባሉ
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ
- ቃላትን በማጣመርና በመነጣጠል ሌሎች ቃላትን ይመሰርታሉ
- ለተሰጡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ
- ስለ መኖሪያ አካባቢያቸው ንጽህና አጠባበቅ ሁኔታ ይገልጻሉ

## ትምህርት አንድ

ያዳመጣችሁትን በሥዕል ታሳያላችሁ

1. **ማነቃቂያ**

መምህር/ት ተማሪዎች ከእንቅልፍ ተነስተው ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት ይጠይቋቸው፡፡ተማሪዎች ፊታቸውን እንደሚታጠቡ፣ጥርሳቸውን እንደሚቦርሹ ጸጉራቸውን እንዲታጠቡ አስረዷቸው

2. **አቅርቦት**

መምህር/ት በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ታሞ ከመማቀቅ ይሻላል መጠንቀቅ የሚል ምንባብ ቀርቧል መምህር/ት የንባቡን ጭብጥ በደንብ ያስረዷቸው፡፡

ንጽህናቸውን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ግንዛቤ እንዲይዙ ያድርጉ

3. **መልመጃዎች**

መምህር ተማሪዎች በምንባቡ መሠረት ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡

1. ተማሪዎች ለምን ጮሁ <u>ጓደኛቸው በመታመሙ</u>
2. ተማሪው የታመመው በምን ምክንያት ነው <u>በንጽህና ጉድለት</u>
3. እናንተ እንደተማሪው እንዳትሆኑ ምን ማድረግ አለባችሁ <u>የግል ንጽህናን በሚገባ መጠበቅ የሚል ሙከራዎችን ከሰሩ በኋላ የተሻለ የንጽህና አጠባበቅ ካለ ይጠይቋቸው በየእለቱ በተገቢው መንገድ ንጽህናቸውን መጠበቅ እንደሚገባቸው ይንገሯቸው፡፡</u>

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

### ሀረጋትን በቅደም ተከተል መጻፍ

1. **ማነቃቂያ**

መምህር/ት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ቆሻሻን እንዴት እንደሚያስወግዱ ይጠይቋቸው፡፡በማቃጠል፣በመቅበር ወይም ደረቅ ቆሻሻን ወደ ማጠራቀሚያ በመውሰድ እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡ ቆሻሻ በአግባቡ መጣል ይገባዋል፡፡ የመሳሰሉ ሀረጋትን ያሰሯቸው፡፡

## 2. አቅርቦት

መምህር/ት ተማሪዎች ስለ ሀረግ ምንነት ይንገሯቸው በምሳሌም ያሳዩአቸው፡፡የቆሻሻ አወጋገድን ሲገልጹ ሀረጋትን እንዲጠቀሙ ያግዟቸው፡፡

ለምሳሌ፡-ቆሻሻን ማቃጠል

1. እጅን በሳሙና መታጠብ
2. ግቢን መጥረግ
3. ወደመጸዳጃ ቤት መሄድ የመሳሰሉትን ያስረዷቸው፡፡

## 3. *መልመጃዎች*

ከስር ባለው ምሳሌ መሠረት ባዶ ቦታዎቹን እንዲሞሉ በማድረግ

ያሰሯቸው

ምሰሌ፡- ግቢን መጥረግ

ቆሻሻን ጉድጓድ መጨመር

ቆሻሻን ማቃጠል

የመልመጃ መልስ

1. ወደ መጸዳጃ ቤት መሄድ
2. ስርዓትን ጠብቆ መጸዳዳት
3. የመጸዳጃ ቤቱን አፍ መክደን
4. እጅን በሳሙናና ውሀ መታጠብ

## ትምህርት ሶስት

## የቃላት ርባታ

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች በምሳሌው መሠረት ሌሎች ቃላትን መስርቱ**

### 1. ማነቃቂያ

መምህር/ት ፊደላትን በመገጣጠም ቃላት ጨዋታ እንዲያደርጉ ያግዟቸው።

ተማሪዎቹም፦

ተ ተማሪ

ዶ ዶክተር

መ መኪና የመሳሰሉትን ሆሄያት የሚጀምሩ ቃላትን እንደጫወታ እንዲከናውኑ ያድርጓቸው።

### 2. አቅርቦት

መምህር/ት ተማሪዎች በምስሌው መሠረት ቃላቱን እንዲመሰርቱ ያድርጉ መምህር/ት የተማሪዎቹን ሰራ በማየት ግብረ መልስ ይሰጧቸው።

### 3. መልመጃዎች

መምር/ት ከላይ በአቅርቦት የተማሯቸውን የቃላት ምሥረታ ሊያጠናክሩ የሚችሉ ሙከራዎችን ይስጧቸው።ከላይ የቀረበውንም በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ።

1.አጠበ፡ አጠብን አሳጠብን

1. አጠበች አሳጠበች አሳጠብን
2. ጠገብን አጠገብን አስጠገብን
3. አጸዳን አጸዳች አጸዳችሁ
4. ጠረግን ጠረገች ጠረጋችሁ

5.በላችሁ አበላችበላችሁ

6.ታጠብን አታጠበች አሳጠባችሁ እያሉ እንዲሰሩ አግዟቸው

## ትምህርት አራት

ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ

1. **ማነቃቂያ**

መምህር/ት ተማሪው መጽሐፍ ላይ ያለውን ሥዕል በማሳየት ያነቃቋቸው፡፡

2. **አቅርቦት**

መምህር/ት ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሠረት የስረዷቸው፡፡

ምሳሌ፡- ሌሊት----ቀን

ነጭ-----ጥቁር

የመሳሰሉትን በመስጠት ተግባራቱን እንዲያከናውኑ ይከታተሉ

3. **መልመጃዎች**

ለሚከተሉት ቃላቶች ተቃራኒ ፍቺ ስጡ

1. ጩኸት ጸጥታ
2. ለስላሳ ሻካራ
3. ብርሀን ጨለማ
4. ሙቀት ቅዝቃዜ
5. ፍርሀት ድፍረት
6. ትልቅ ትንሽ
7. ንጹህ ቆሻሻ
8. ተራራ ሜዳ
9. ሰማይ ምድር
10. ረሀብ ጥጋብ የመሳሰሉትን ያሰሯቸው፡፡

## ትምህርት አምስት

## የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ

### 1. ማነቃቂያ

መምህር ባለፈው የተማሩትስለምን እንደሆነ ይጠይቋቸው፡፡ በማስከተል የእለቱን ርእሰ ጉዳይ "በቁማችን ሞተናል" በሚል ርእስ ምንባብ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው፡፡

### 2. አቅርቦት

መምህር/ት ቀጥሎ ስለአካባቢ ንጽህና የሚያስረዳውን ጽሑፍ ያስረዷቸው፡፡ እርስዎም ሲያነቡ ተማሪዎቹን መከታተላቸውን ለማረጋገጥ አንዱን አረፍተ ነግር አንብበው ሲጨርሱ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የመጀመሪያው አረፍተ ነገር ስለምን ያወራል በማለት ይጠይቋቸው፡፡ በዚህም መሠረት ሲያነቡ ለጠየቁት ጥያቄ አብዛኛው ተማሪ ካልመለሰ እያዳመጡ አይደለም ወይም የአዳምጦ መረዳት ችግር ስለሚኖር ደጋግመው ማንበብ ይጠበቅብዎታል፡፡

### 3. መልመጃዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ

1. አቶ ምንተስኖት "በቁማችን ሞተናል" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?
   በቆሸሸ በተበከለ አካባቢ ስለሚኖሩ ነው፡፡
2. አቶምንተስኖት እጃቸውን ያወናጨፉት ለምንድነው?
   በአካባያቸው መበከል ስለተበሳጩ የመሳሰሉትንና በሁለተኛው ጥቄ የቀረበውን በምሳሌው ,መሠረት ጻፉ፡፡

**ምሳሌ**

ጥፍር መቁረጥ ቆሻሻን መሰብሰብ

**ክፍለ ትምህርት ስድስት**

**የግል ንጽህና**

**የአካባቢ ንጽህና**

ፊትን መታጠብ ቦይ ማበጀት

ጸጉር መታጠብ ቆሻሻን ማቃጠል

ልብስ ማጠብ ጎዳና መጥረግ

ጸጉርን መታጠብ ጥርስ መፋቅ

ቦይ ማበጀት ቆሻሻን ማቃጠልና የመሳሰሉት

# ትምህርት ሰባት

## አዳዲስ ቃላትን በማጣመር መጻፍ

1. **ማነቃቂያ**


   መምህር/ተ ተማሪዎቹን በቀላሉ ወደ ትምህርቱ እንዲገቡ ለማድረግ ተረት ይንገሯቸው

2. **አቅርቦት**

   **ስለ ጥምር ቃላት ማብራሪያ ያስፈልጋል።**


   መምህር/ት ቀትሎ የቀረበውን ቃል በምሳሌው መሠረት ያሰሯቸው።

   ምሳሌ፡- ቤተ-ክርስቲያን---ቤተ ክርስቲያን




3. **መልመጃዎች**

   መምህር ቀደም ብሎ በቀረበው መግለጫ መሠረት ቃላትን በማጣመር ሌሎች ቃላትን ይጻፉ።




የመሳሰሉትን ቃላት ያሰሯቸው።

1.ዳቦ ቤት 2.ብረት ድስት 3.ፍርድ ቤት 4.

## ትምህርት ስምንት

### ቅጥያዎችን በመነጠልቃልን ነጻ ማድረግ

1. **ማነቃቂያ**

ያለፈው እለት ትምህርት ስለምን እንደነበር ይጠይቋቸውና የእለቱን ትምህርት ርዕሰ ጉዳይ ያስተዋውቁ

2. **አቅርቦት**

መምህር/ት በተማሪው መጽሐፍ የቀረቡትን ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ያስረዷቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| አበጠረች | አበጠረ | ች |
| አጸዳች | አጸዳ | ች |

3. **መልመጃዎች**

መምህር ከላይ በተማሩት መሠረት ቅጥያዎቹን በማውጣት ጾታውን ከሴት ወደ ወንድ ቀይሩ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. አለበሰች | አለበሰ | ች |
| 2. አነጠፈች | አነጠፈ | ች |
| 3. አመጣች | አመጣ | ች |
| 4. ቦረሸች | ቦረሸ | ች |
| 5. ቆረጠች | ቆረጠ | ች |
| 6. በላች | በላ | ች |

## ትምህርት ዘጠኝ

ፊደላቱን በማስገባት ቃላትን መመሥረት

1. **ማነቃቂያ**

   መምህር/ት በመጽሐፍ የቀረበውን ሆሄ እርስዎ ያንብቡላቸው፡፡

   ተማሪዎችም አዳምጠው እንዲናገሩ በማድረግ ሆሄያቱን አስታውሱ፡፡

2. **አቅርቦት**

መምህር/ተ ተማሪዎች በሰንጠረዡ የሰፈሩትን ሆሄያት በማስገባት ቃላት እንዲመሰርቱ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ሆሄያትን በማቀናጀት ቃላት እንዲመሰርቱ ይርዷቸው፡፡

3. **መልመጃዎች**

መምህር/ት ከላይ በአቅርቦት በተሰጠው ምሳሌመሠረት ቃላቱን እንዲያሟሉ ይረዷቸው፡፡

ሀ. --ለቀ ወለቀ

ለ. --መረ ጀመረ

ሐ. --ረሰ ደረሰ

መ. ለቀ - ለቀመ

ሠ. --ለቀ ፈለቀ

ረ. ወረ - ወረደ

ሰ. ደረ - ደረሰ

ሸ. ሰ- ሰጠ

ቀ. ደ- ደጅ

በ. ል- ልጅ

የመሳሰሉትን ያሰሯቸው፡፡ በቤታቸውም እንዲለማመዱ ይዘዟቸው፡፡

# ክፍለ ትምህርት አስር

**ቁጥሮችን መለማመድ**

**ዓላማ፡- ቁጥሮችን ማንበብ**

1. **ማነቃቂያ**

መምህር/ት ተማሪዎችን "አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች በግርግዳ ላይ"የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡

2. **አቅርቦት**

መምህር/ት ተማሪዎችን (1)--አንድ (2) ሁለት (3) ሶስት (4) አራት (5)አምስት (6) ስድስት (7) ሰባት (8) ስምንት (9) ዘጠኝ (10)አስር እየሉ ቁጥሮችን በአህዝ እንዲያስቀምጡ ያግዟቸው፡፡

3. **መልመጃዎች**

መምህር/ት ከታች በ ሀ ረድፍ የቀረቡትን ቁጥሮች በለ ክፍልካሉት አህዝ ጋር አዛምዱ

1. 10 (ሰ) አስር
2. 20 (ሽ) ሀያ
3. 30 (በ) ሰላሳ
4. 40 (ረ)አርባ
5. 50 (ቀ) ሀምሳ
6. 60 (ሐ) ስልሳ
7. 70 (ሀ)ሰባ
8. 80 (መ)ሰማኒያ
9. 90 (ሡ) ዘጠና
10. 100 (ለ) መቶ እያሉ ደጋግመው እንዲሰሩ ያድርጉ

### 4. ማበልጸጊያ

በማበልጸጊያ ተግባራት የቀረቡት መልመጃዎች በምእራፍ የቀረቡትን ትምህርቶች ለማጠናከር የቀረቡ ናቸው በመሆኑም እነዚህን መልመጃዎች ተማሪዎች በግላቸው እንዲሰሯቸው ያድርጉ፡፡ የማበልጸጊያ መልመጃዎች በየክፍለ ትምህርቱ የቀረቡ ስለሆነ ተማሪዎች የሚሰሩትንና እርስዎም የሰሩትን ለማመሳከር እንዲረዳዎት ተቀምጧል፡፡ ተግባራቱን በየቤታቸው፣ በክፍል ውስጥም እንዲያከናውኑ ደጋግመው አንብበው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

### 5. መርጃ መሳሪያ

በአካል ቅረብ የሚቻሉትን እንደ ሳሙና ውሀ ኳስ የመሳሰሉትን በተግባር በማሳየት በሥዕል በማስደገፍ በቪዲዮ በማስደገፍ በማሳየት ማስተማር ትምህርቱን ተጨባጭ እንዲሆን ይረዳል፡፡

### 6. ግምገማ

ንጽህናን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ከጓደኞቻቸው ጋር በተግባር እንዲያሳዩና ያዳመጡትን ምንባብ ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅና ምንያህል ውጤጣማ እንደሆነ ይፈትሹ፡፡ ቃላትን በመጠቀም የንጽኅና አጠባበቅ ዘዴዎችን ይዘርዝሩ፡፡ ንጽህናን ካለመጠበቅ የሚመጡ ጉዳዮችን በዝርዝር እንደተረዱ ያረጋግጡ፡፡ በጽሑፍና በንባብ የሚሰሩ መልመጃዎችን ማጠቃለያና ማበልጸጊያ ተግባራትን ደግሞ የቤት ስራ በመስጠት ሰርተው ክፍል ውስጥ እንዲቀርቡ በማድረግና ማስተካከያ በመስጠት ግምገማው ሲካሄድ የትምህርቱን ስኬታማነት ለመገምገም ያስችላል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## ሥነ ምግባር

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የመልካም ሥነ ምግባር መመሪያን ይገልጻሉ፡፡
- መምህሩ የሚነያቡላችሁን በማዳመጥ ጥቂዎችን ይመልሳሉ፡፡
- የቃላትን ፍቺ እና ተዛማጅ ቃላትን ይለያሉ፡፡
- ቃላትን በመጠቀም ነጠላ አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- ብዙና ነጠላ ቁጥሮችን ይለያሉ፡፡
- ቃላትን በቅደም ተከተል ያደራጃሉ፡፡

### <u>ትምህርት አንድ</u>

### <u>አዳምጦ መናገር</u>

<u>**1. ማነቃቂያ፡-**</u> መምህር ተማሪዎች ጓደኞቻቸውን ታላላቆቻቸውን ቤተሰባቸውንና የማህበረሰቡ ከበሬታ ይገባቸዋል የተባሉትን እንዴት ማክበር እንደሚገባቸው ይንገሯቸው፡፡

<u>**2. አቅርቦት፡-**</u> መምህር ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች በእርጋታ ያንብቡላቸው

**ክብር ስጡ**

አንድ ቀን አንድ አዛውንት ብዙ እቃ በትከሻቸው ተሸክመው ይሄዳሉ፡፡ ከኋላቸው ፍቅርተና ጀማል ከትምህርት ቤት ወደ ቤታቸው ሲሄዱ አዛውንቱን ከሩቅ አዩዋቸው፡፡ አዛውንቱ ትንሽ ሄደው ይቀመጣሉ፡፡ ፍቅርተና “ጀማል አባባን አየሃቸው?” በማለት ለጀማል አሳየችው፡፡ “ማናቸው አባባ?” ኦ! እኒያ ብዙ እቃ የተሸከሙትን ነው?” “አዎ!”****”

**ፍቅርተ አዛውንቱ ለጀማል ካሳየችው በኋላ ጀማል ምን የሚል ይመስላችኋል?”*****

“እና ምን ላድርግ? ቀድሜ ነው ያየኋቸው፡፡ ለራሴ ርቦኛል፡፡ የአንቺ ነገር እኮ! ስለራበኝ ነው እንጂ ሳያሳዝኑኝ ቀርተው አይደለም” ብሎ መለሰላት፡፡ ፍቅርተም “ግድ የለም በል ና! እንድረስላቸውና የያዙትን እቃ ተቀብለን እንሸኛቸው” በማለት እየሮጡ ወደ ሽማግሌው ሄዱ፡፡

<u>3. ***መልመጃዎች*** **፡-**</u> ከምንባቡ የተወጣጡ ጥያቄዎችን ይመልሱ፡፡

1. ፍቅርተ ለጀማል፡ ያሳየችው ምንን ነው? እቃ ተሸክመው የደከማቸው አዛውንት

2. አዛውንቱ ምን ይዘው ነበር? ብዙ ዕቃዎችን

3. ፍቅርተና ጀማል፡- ምን አደረጉ? ዕቃውን አገዟቸው፡፡

የመሳሰሉት ካዳመጡት እንዲመልሱ ያድርጉ ፡፡

**ትምህርት ሁለት**

**<u>ለቃላት ፍቺ ይሰጣሉ</u>**

**<u>1. ማነቃቂያ</u>** መምህር/ት እርሰዎ ሰላምታ ሲሰጡ ተማሪዎች ቆመው መልስ ሊሰጡ ለምን ተነሳችሁ ብለው በመጠየቅ፡ እንደየ አካባቢው ባህል ማክበር ስለሚገባቸው ነበርና በማክበራቸው ከማህበረሰቡ የሚሰጣቸውን ምላሽም ይንገሯቸው ። ተባረኩ ፤ ትልቅ ደረጃ ድረሱ

**<u>2. አቅርቦት ፡-</u>** ላይ የተቀመጡትን ቃላት ፊቺ እንዲናገሩ በማድረግ የቃላት እውቀታቸውን እያዳበሩ እንዲሄዱ ይረዳቸዋል፡፡

የቀረቡት ቃላት ተሸከሙ፡-

1. አዘሉ፡ <u>በትከሻቸው ጫኑ</u>
2. አሣያት፡ <u>አመለከታት</u>
3. አዘኑ ፡ **<u>ተከፉ</u>**
4. ረዳ ፡ **<u>አገዘ</u>**
5. ተቀበለ፡ ወሰደ፡ የመሣሠሉትን ይሰራሉ

3. መምህር/ት የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን ስጡ፡፡ ይበሉና የቃላቱን ፍቺ በደብተራቸው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

**<u>ምሳሌ</u>** ሰጠ ፡ ቸረ፡ ለገሰ"

1. **ኀበዝመለሰ**፡ **<u>ግብረ መልስ ሰጠ</u>**

## ትምህርት ሶስት

## ነጠላ ዓ.ነገር መመሠረት

### ስለነጠላ

1. **ማነቃቂያ፡-** መምህር/ት ቀጥሎ የቀረበው ተግባር ከማከናወናቸው በፊት አንድ ተማሪ በማሥነሳት ወደ በር እንዲሄድ ያድርጉ፡፡ ለተማሪዎች ልጁ ምን እያደረገ እንደሆነ ይጠየቁ የተማሪዎች መልስ ወደ በሩ እየሄደ ነው፡፡ እያሉ ነጠላ አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ያደርጉና ያነቋቋቸው፡፡
2. **አቅርቦት፡-** መምህር/ት ከታች የቀረቡትን ቃላትና ተግባራት የሚገልጹ ሥዕሎች በመመልከት ነጠላ ዐ.ነገር እንዲመሰርቱ ያግዟቸው በምሳሌም በማስደገፍ እንዲሰሩ ያግዟቸው ፡፡

**ልምሳሌ፤-** ሸለመ ፡- **ጎበዝ ተማሪ ተሸለመ**

1. **ጎበዝ** 1. አባት ጎበዝ ልጁን ሸለመ፡፡
2. **መከረ** 2. መምህር ተማሪዎችን መከረ፡፡
3. **ተወደደ** 3. የተማሪው ስራ ተወደደ፡፡
4. **ረዳ** 4. ተማሪው አቅመ ደካማውን ረዳ
5. **አጨደ** 5.ገበሬው ጤፉን አጨደ፡፡ የመሳሰሉትን ተግባራት እንዲሰሩ ያግዟቸውና ሥራውን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

3. **መመህር/ት፡-**ተማሪዎች ከላይ ከተማሩት መሠረት ከ1- 5 ባሉት ቃላት ነጠላ ዐ.ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ

1. **ቀቀለ**፡- ማዶ ጎመን ቀቀለች ፡፡
2. **ገዛች**፡- ደራሮ ልብስ ገዛች፡፡
3. **ታመመ**፡- አበበ በድንገት ታመመ፡፡
4. **ተከሰ**፡- አበባው ሚካኤል ተከሰ፡፡
5. **ቀለጠ**፡-ሳሙናው በውሃ ቀለጠ፡፡

## ትምህርት አራት

### ሥዕሉን በማየት ነጠላ ዐ.ነገር መመሥረት

1. **ማነቃቂያ :-** መምህርት ለተማሪዎች የተለያዩ ቁሶችን በማሳየት ብዛታቸውን የሚገልጽ ቃል እንዲመሰርቱ ያድርጉ

   **ለምሳሌ** ሰው፡**ሰዎች** ፡ ተማሪ ፡ **ተማሪዎች** በር ፡ **በሮች** የመሳሰሉት ይተግብሩ፡፡

2. **አቅርቦት :-** መምህር ተማሪዎች በተማሪው መጽሐፍ ያለውን ብዛት ገላጭ ሥዕል ያሳዩአቸው ሥዕሉን በማየት ብዛታቸውን የሚገልጽ ነጠላ ዐ.ነገር እንዲሰሩ ያድርጉ የሰሩትን ለጓደኞቻቸው ያሳዩ፡፡

3. **መልመጃዎች**፡- ከላይ በቀረቡት ሥዕሎች የሚታዩትን ብዛት አመልካች ነጠላ ዐ.ነገር በመጠቀም የሚል ነው፡፡

   ለምሳሌ

1. ሁለት በጎች በሜዳ አሉ ፡፡
2. ተማሪዎች እየተጫወቱ ነው፡፡
3. ልጁ ወደ ት/ቤት እየሄደ ነው፡፡
4. መምህሩ አዳዲስ ኳሶችን ይዘዋል፡፡
5. አዳዲስ ብርጭቆዎችን ሰጠኝ ፡፡
6. መኪናዎቹ ያምራሉ፡፡

## ትምህርት አምስት

## ትዕዛዝን መተግበር

1. **ማነቃቂያ**፡- መምህር ለተማሪዎችዎ የመልካም ስነ-ምግባርና የመጥፎ ሥነ-ምግባር ልዩነቶች ያብራሩ፡ በተግባር በክፍል ውስጥም ያሳዩ መልካም ሥነ-ምግባርና የመጥፎ ሥነ-ምግባር ልዩነትን ያስረዷቸው፡፡
2. **አቅርቦት**፡- መምህር ተማሪዎችን በየምድቡ ይክፈሏቸው በመጥፎና በመልካም ሥነ-ምግባር በመክፋፈል ቃላቱ በየምድባቸው እንዲከፈሉ ያደርጉ፡፡

መስረቅ አውጥተን መናገር

አለመታዘዝ ሀቀኝነት

መዋሸት ሰውን ማክበር

መሳደብ ታማኝነት በሚሉ ምድቦች ይመድቧቸው፡፡

3. **መልመጃዎች**

**ጥሩ ሥነ-ምግባርመጥፎ ሥነ-ምግባር**

- እውነት መናገር - መስረቅ
- ሰውን ማክበር - መዋሸት
- መታዘዝ - ለራስ ቅድሚያ መስጠት
- ሀቀኝነት - መሳደብ ፡ የመሳሰሉትን እንዲሰሩ

በማድረግ ስለ መልካም ሥነ-ምግባር ማስተማር ይቻላል፡፡

## ትምህርት ስድስት

## ቃላትን በማስተካከል ዐ.ነገር መጻፍ

1. **ማነቃቂያ** :- መምህር/ት ተማሪዎቹ እንዲነቃቁና ተግባራቱን እንዲያከናውኑ የተዘበራረቁ ቃላትን ይስጧቸው **ምሳሌ** :- መምህራንን እወዳለሁ በጣም
   - መምህራንን በጣም እወዳለሁ።
2. **አቅርቦት:-** መምህር ተማሪዎች የተዘበራረቁ ቃላትን እያስተካከሉ ዐ.ነገር እንዲጽፉ ያግዟቸው።

   **መመሪያ:-** ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ተዘበራርቀው የተቀመጡ ቃላትን በቅደም ተከተል ጻፉ።

1. አዛውንቱን እርዷቸው በስራ
   - አዛውንቱን በስራ እርዷቸው።
2. ርዕስ መምህራችን ሰበሰቡን ዛሬ
   - ርዕሰ መምህራችን ዛሬ ሰበሰቡን።
3. ተሸከመ እቃ አበበ
   - አበበ እቃ ተሸከመ ።
4. አበበን አገዝኳቸው ወጪ
   - አበበን ወጪ አገዝኳቸው።

3. **መልመጃዎች:-** የሚከተሉትን ቃላት ወደ ነጠላ ቁጥር ቀይሩ።

   **ለምሳሌ:-** ዝሆኖች- ዝሆን

   1. ዘመዶች : ዘመድ
   2. ዝማሬዎች: ዘማሬ
   3. ልጆች: ልጅ
   4. አይነቶች: አይነት

## ትምህርት ሰባት

## ዐ.ነገር መስርቱ

1. **ማነቃቂያ፡-** መምህር ስለ ጉርብትና ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ጠይቋቸው፡፡
2. **አቅርቦት፡-** መምህር በተማሪው መጽሐፍ የቀረበውን አብሮ መኖር የሚል ምንባብ ካነበቡ በኋላ ከምንባቡ የወጡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
3. **መልመጃዎች ፡-**
   1. አብሮ መኖር ምን ይጠቅማል? ማህበራዊ ህይወትን ያጠነክራል
   2. ማህበራዊ ሕይወት እንዴት ይጎልብታል? በሰዎች መካከል መከባበርና መቻቻል ሲኖር ነው
   3. ጥሩ ጎረቤቶች በበዓል ቀን ምን ያደርጋሉ?

## ትምህርት ስምንት

## የመልካም ሥነ ምግባር መገለጫዎችን መገንዘብ

1. **ማነቃቂያ፡-**መምህር ተማሪዎች ሥለ መልካም ሥነ ምግባር ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ይጠይቋቸው፡፡
2. **አቅርቦት፡-**

   መምህር/ት ተማሪዎች ከታች የበቀረቡትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

   1. ቅንነት

   2.አያስፈልግም

   3.ሀቀኝነት፣ምስጢር ጠባቂነት፣ታማኝነት፣አርዓያ መሆንና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**በሚከተሉት ቃላት ዐ.ነገር ስሩ።**

1. **ተጋገዙ፡-** ከጎረቤቶችዎ ጋር አከባቢን ለማጽዳት ተባበሩ
2. **መከባበር፡-** ሰዎች በሰላም ለመኖር ሲሉ ይከባበራሉ።
3. **ተማመኑ፡-** በለሙና ደንድር በሰላም ለመዋር ተማመኑ
4. **ተቻቻሉ፡-** ጎረቤቶች በሰላም ለመኖር ሲሉ ባህሪያቸውን ተቻቻሉ

3. **መልመጃዎች ፡-** በቡድን በመወያየት በምሳሌው መሠረት ዐ.ነገር መስርቱ የሚል ትዕዛዝ ቀርቦለችኃል ።
1. **መተማመን ፡-** ሰዎች በሰላም ለመኖር መተማመን አለባቸው።
2. **አብሮ መኖር ፡-** ሰዎች አብረው ለመኖር መቻቻል አለባቸው።
3. **መተሳሰብ፡-**ይህን ክፉ ጊዜ በመተሳሰብ ማሳለፍ ያስፈልጋል።

**ትምህርት ዘጠኝ**

**የሥነ-ምግባር መገለጫዎች የሚገልጽ ዐ.ነገር ይሰራሉ**

1. **ማነቃቂያ ፡-** መምህር ተማሪዎችን ያለፈውን እለት ትምህርት ምን እንደ ሆነ ይጠይቋቸው የዕለቱን ትምህርት ያስተዋውቁ።
2. **አቅርቦት፡-** መምህር የመልካም ሥነ-ምግባር መገለጫዎች የሚል ምንባብ ያንብቡላቸው ምን ያህል ምንባቡን እንደተገነዘቡ ይጠይቋቸው ስለ መለመልካም ሽነ ምግባር እንዲረዱ ያድርጋቸው ጠቀሜታውንም በሚገባ ይንገሯቸው።
3. **መልመጃዎች፡-** መምህር የመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተውጣጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ
   1. ከመልካም ሥነ-ምግባር መርሆች ከአንዱ ጥቀሱ :**ሀቀኝነት**
   2. የሰውን ንብረት ሳይፈቅዱ መንካት ያስፈገልጋል ፡ **አያስፈልግም**
   3. ሌሎች የሥነ-ምግባር መርሆችን ጥቀሱ አደራን ተቀብሎ በአግባቡ መያዝ የሰውን ንብረት አለመንካት አለመሳደብ ለታላላቅ ቅድሚያ መስጠት ወዘተ ናቸው ።

# ትምህርት አስር

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- ሀሳብን በጽሑፍ መግለጽ

### የሥነ-ምግባር መገለጫዎችን ብጽሑፍ መግለጽ

1. ማነቃቂያ፡- መምህር ተማሪዎች የሥነ-ምግባር መገለጫዎችን በየተራ እየተነሱ ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ

2.አቅርቦት ፡- መምህር ለተማሪዎቹ ባለፈው ትምህርት በተማሩት መሠረት ግንዛቤያቸውን ለማጠናከር ማብራሪያ ይሰጣቸው፡፡ በመቀጠል ፊደላትን በማነጣጠል ቃላት እንዲመሰርቱ ምሳሌ ይሰጣቸው፡፡

ምሳሌ ፡- ተሰጠ - ተ - ሰጠ

1. **ተወደደ** .................ተ - ወደደ

2. **ተቆጣ** ...................ተ - ቆጣ

3. **ተከመረ** .................ተ - ከመረ

4. **ተሰደበ** ..................ተ - ሰደበ

3. መልመጃዎች፡-

እስካሁን የተማራችሁትን የሥነ-ምግባር መገለጫዎች ዘርዝሩ ፡፡

1. ሀቀኝነት ፡- የእውነት ሰው መሆን አለመዋሸት

2. ታማኝነት ፡- አደራን ተቀብሎ በአግባቡ መወጣት

3. ሰዎችን ማክበር ፡- አለመስደብ ለታላላቅ ቅድሚያ መስጠት ፤መታዘዝ ፤ጓደኛን ፤መውደድ የመሳሰሉትን ያሰፈርቸው ፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

### የአመጋገብ ሥርዓት

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ✓ መሠረታዊ ቃላትን ይናገራሉ፡፡
- ✓ በምንባቡ መሠረት በቃላቸው መልስ ይሰጣሉ፡፡
- ✓ ቀለማትን ይለያሉ፡፡
- ✓ አረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ፡፡
- ✓ የመመገቢያ እቃዎችን እና አገልግሎታቸውን ይገልጻሉ፡፡
- ✓ ሥርዐተ ነጥቦችን በትክክ ትገልጻላችሁ ይጠቀማሉ፡፡
- ✓ ፊደላትን በክፍት ቦታዎች በመሙላት ቃላትን ይመሰርታሉ፡፡
- ✓ በሚሰጣቸው ምሳሌ መሠረት ቃላትን በየምድባቸው ያስቀምጣሉ፡፡
- ✓ የፊደላትን ቦታ በማቀያየር ወይም በመቀነስ ቃላትን ይመሰርታሉ፡፡
- ✓ ፊደላትን በማጣመር ቃላትን ይጽፋሉ፡፡
- ✓ በተሰጣቸው ቃላት ዓረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

## ትምህርት አንድ

**<u>ምንባቡን በማዳመጥ ይመልሱ፡፡</u>**

1.ማነቃቂያ ፡- መምህር/ት ተማሪዎች ወደ ት/ቤት ከመምጣታቸው በፊት ቁርሳቸውን መብላት እንዳለባቸው ይንገሯቸው፡፡ በመቀጠል ስለተመጣጣኝ ምግቦች ይጠይቋቸው፡፡

2. አቅርቦት፡- መምህር በተማሪው መጽሐፍ የቀረበውን የተመጣጠኑ ምግቦች አስፈላጊነት የሚለውን ምንባብ ያንብቡላቸው በሚያነቡበት ወቅት የተማሪዎቹን መረዳት ለማረጋገጥ ቆም እያሉ ምን ተረዳችሁ እያሉ ይጠይቋቸው፡፡ ማብራሪያም ይስጧቸው ለምን እንደሚጠቅሙ ይጠይቋቸው፡፡

3. መልመጃዎች፡- መምህር ለተማሪዎቹ ምንባቡ ምንበባቸውን ለማረጋገጥ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን ያስሯቸው፡፡

1. ተመጣጣኝ ምግቦች በስንት ይከፈላሉ? **<u>በሦስት ይከፈላሉ</u>**

2. ገንቢ ምግቦች የሚባሉትን መልሱ እንቁላል ' አሳ ' ሥጋ ' አይብ ' አተር ' ባቄላ ' የመሳሰሉት ናቸው፡፡

3. በሽታን ተከላካይ ምግቦችን ግለጹ ፡- ብርቱካን ሎሚ ' ፓፓያ ' መንደሪን ' ሙዝ ' ትርንጎ. እንደሆኑ ያስረዷቸውና ስህተት ካለ ያስተካክሏቸው፡፡

## ትምህርት ሁለት

### <u>መስረታዊ ቃላትን መናገር</u>

1. ማነቃቂያ፡- ተማሪዎች ስለ ምግብ አይነቶች እንዲናገሩ ያድርጉ ለምሳሌ፡ እንቁላል ' ዳቦ ' ወተት ' ድንች ' በቆሎ ' ካሮት ' ሙዝ ' ብርቱካን ' ጎመን ' የመሳሰሉትን እንዲዘረዝሩ ያድርጉ፡፡

2. አቅርቦት፡- መምህር ለተማሪዎች የምግብ አይነቶችን የያዘ ሥዕል አለ፡፡ ሥዕሎችን በደንብ ያሳዩዋቸው ፡፡

ሥዕል

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| እንቁላል | አሳ | ወተት | ሙዝ<br>ብርቱካን | ዳቦ | በቆሎ | ጎመን | ካሮት |

3. መልመጃዎች፡- መምህር ከላይ በቅርበት ሥዕሎች በየክፍላቸው በመዘርዘር በቃል ተናገሩ፡፡

1. ሃይልና ሙቀት ሰጪ ..................................................................................

2. በሽታን ተከላካይ ምግቦች ፡- <u>ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ፓፓያ ፣መንደሪንሙዝ ፣ ትርንጎ</u>

3. ገንቢ ምግቦች ፡- <u>እንቁላል' አሳ 'ሥጋ 'አይብ 'አተር 'ባቄላ</u>

በክፍላቸው እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

## ትምህርት ሶስት

### ቀለማትን መለየት

1. **ማነቃቂያ፡-** መምህር/ት በመጀመሪያ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ እንዲመለከቱ ካደረጉ በኋላ በመጽሐፍ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንነት ስንት ቀለማት እንዳሉትና የቀለማቱን ስም በመጠየቅ ምላሽ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ስለ ኢትዮጵያ ባንዲራ የቀረበውን መዝሙር እርስዎ ሲያነቡላቸው በማዳመጥ በጋራ ደጋግመው እንዲዘምሩ በማድረግ ያነቃቋቸው፡፡

2. **አቅርቦት፡-** በመጀመሪያ በመጽሐፉ የቀረቡትን የቀለም አይነቶች የሚገልጹ ቃላትን እርስዎ ሲያነቡ ተማሪዎች እያዳመጡ በጋራ እንዲለዩ ያድርጉ ቀጥሎ የቀለም አይነቶች የቀደመ እውቀታቸውን መሠረት በማድረግ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ ተማሪዎቹ ከሞከሩ በኋላ የቀለማቱን ስም ከቀለማቱ ጋር በማጣመር እርስዎ ሲጠሩ እነሱ እየተከተሉ በጋራ እንዲጠሩ በማድረግ ያለማምዷቸው፡፡

3. **መልመጃዎች፡-** መምህር/ት ተማሪዎች የቀረቡትን ሰዕሎች ስምና ቀለም እንዲናገሩ ያድርጉ ፡፡ በዚህ ላይ ተማሪዎች የራሳቸውን እርሳስና እስክሪብቶ ቀለም በመጠቀም የእግረኛ መንገድ ምልክት ከለር በመጠቀም ባንዲራ እንዲሰሩ ያድርጉ ፡፡ በመቀጠል ከላይ የቀረበውን ሥዕል እየተመለከቱ ቀለማቱን በጽሑፍ ይግለጹ፡፡

1. አረንጓዴ ቀለም
2. ቀይ ቀለም
3. ቢጫ
4. ጥቁር
5. የእግረኛ መሳለፊያ
6. ቀይ ቢጫ አረንጓዴ

## ትምህርት አራት

## ቃላትን በማቀናጀት ዐ .ነገር መጻፍ

1. **ማነቃቂያ** ፡- መምህር/ት ማነቃቂያው ግልጽ እንዲሆንላቸው ለመጀመሪያ እርሰዎ በቀላል ወደ ክፍል ሊመጣ የሚችል የምግብ (መዝ÷ብርቱካን ) ቢያንስ አንድ በማምጣት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ያድርጉ ፡፡ ቀጥሎም በተማሪው መጽሐፍ የቀረበውን የምግብ ሥዕል ተመልክተው የምግቦቹን አይነት እንዲናገሩ በማድረግ ያነቋቋቸው፡፡

2. **አቅርቦት፡-** መምህር/ት 1-5 የቀረቡትን ቃላት ዐ.ነገር ስሩባቸው፡፡

1.ባቄላ፡- ባቄላ እሸት ይበላል

2. ወተት፡- ዛሬ በጠዋት ወተት ጠጣሁ

3. አሳ፡- አሳን መመገብ ጠቃሚ ነው

4. ፓፓያ፡- ከበደ ፓፓያ በላ

5. አትክልት ፡- ከበደ አትክልት መመገብ ይወዳል፡፡

3. **መልመጃዎች፡-** ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ዐ.ነገርን በመጠቀም መልስ ይስጡ፡፡

**ምሳሌ፡-** 1. ጤናማ አመጋገብ ለምን ይጠቅማል?

2. በስለው የሚበሉ ምግቦችን በጥሬያቸው ብንመገብ ምን እንሆናለን?

3. ሥጋ፡ ሥጋን በመጠኑ አብስሎ መመገብ ያስፈልጋል፡፡

4. ብርቱካን ፡አበበ ብርቱካን ይወዳል፡፡

5. ሰላጠ ፡ እናቴ ሰላጣ ትወዳለች

## ትምህርት አምስት

## <u>የቤት ዕቃዎችን አገልግሎት መግለጽ</u>

1. **<u>ማነቃቂያ፡-</u>** መምህር/ት ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ሥዕሎቹን በመመልከት አገልግሎታቸውን ይግለጹ፡፡ ለምን ይጠቅማሉ?፡፡

| ሰፌድ | አክንባሎ |
| --- | --- |

-ለእንጀራ ማስቀመጫ ለዳቦ መያዣ ያገለግላል፡፡

-አክንባሎ እንጀራ ለመጋገር ምጣድ ለመክደን፡፡

2. **<u>አቅርቦት፡-</u>** መምህር/ት ተማሪዎች ከታች የቀረበውን ሥዕል ተመልክተው ስማቸውን እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ እርስዎም ስማቸውን በትክክል መግለጻቸውን ያረጋግጡ፡፡

| | |
| --- | --- |
| 1. ሳህን | 4. ብርጭቆ |
| 2. ድስት | 5. ኩባያ |
| 3. ማንኪያ | 6. ትሪ |

**<u>መልመጃዎች፡-</u>** መምህር/ት ተማሪዎች ከታች የቀረቡትን ቃላት አገልግሎት በዓረፍተ ነገር ይግለጹ፡፡

1.ድስት፡- አለሚቱ በሸክላ ድስት ወጥ ሰራች፡፡

2. ቢለዋ፡- ደራሮ በቢለዋ ሽንኩርት ከተፈች፡፡

3. ማንኪያ፡- ቦንከላ በማንኪያ ክትፎ በላ፡፡

4. ማጥለያ፡- አልማዝ ቅቤውን በማጥለያ አጣራች፡፡

5. ሳህን፡- ነጋዴው የተሰበረ ሳህን ሸጠልኝ፡፡

## ትምህርተ ስድስት ፡

## ሥርዓተ ነጥብ

1. **ማነቃቂያ፡-** መምህር/ት ባለፈው ክፍል ትምህርት ሰለሞን እንደተማሩ ይጠይቋቸው በማስቀጠልም (፡ ፣ ? ! ፡፡) አገልግሎት ይጠይቋቸው፡፡

2. **አቅርቦት፡-** መምህር ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ የቀረበውን ምንባብ ካነበቡ በኋላ በምንባቡ ውስጥ አገልግሎት የዋሉትን ስርዓተ ነጥቦች ለይተው ያውጡ፡፡ በምንባቡ ውስጥ የተገለጹት ሥርዓተ ነጥቦች

(፥) ነጠላ ሰረዝ ፡- ተመሳሳይነት ያላቸውን ቃላት ለመለየት፡፡

(፡) ቃለን ከቃል ለመለየት፡፡

(ተያዥነት ያላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ ሐሳቦችን በአንድነት አብታትሎ ለማቅረብ ያገለግላል፡፡

(፡፡) ለሀሳብ መቋጫነት ያገለግላል፡፡

(?) ለጥያቄያዊ ዐ.ነገር ያገለግላል የሚሉት ናቸው፡፡

መልመጃዎች፡- በምንባቡ ውስጥ የቀረቡትን ስርዓተ ነጥቦች ለይተው እንዲያወጡ ያድርጉ፡፡

(፡)

(፡፡)

(፤)

(?)

ናቸው፡፡

## ትምህርት ሰባት

### ፊደላትን በማሟላት ቃላት መመሥረት

1. **ማነቃቂያ፡-** - ተ - ተወደደ ---- ተበላ -- ተነገረ ፡- ተተካ ፡ የመሳሰሉትን ቃላት ስሩ፡- ቃላቱ፡ ተ - ወደደ፡ - ተ - በላ - ነገረ - ተካ

2. **አቅርቦት፡-** መምህር ቀጥሎ ያልተሟሉ ቃላት ቀርበዋል ከሰንጠረዥ ውስጥ ተስማሚ ሆሄያትን በመምረጥ አሟሉ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ባ | ት | ን | ም | ሰ | ሽ |
| ብ | ማ | | | | |

1.ኩ ባ ያ 5. ሲ ኒ

2. ድስ ት 6. ሹ ካ

3. ማ ን ኪያ 7. ብ ርጭቆ

4. ም ጣድ 8. ማ ማሊያ በማለት መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡

**መልመጃዎች፡-** መምህር ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም ዐ.ነገር እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

1. ኩባያ፡- አባባ በኩባያ ውሃ ጠጡ፡፡
2. ድስት፡- ሚሻሜ በሸክላ ድስት ወጥ ሰራች፡፡
3. ማንኪያ፡- ገንፎ በማንኪያ ይበላል፡፡
4. ምጣድ ፡- እናቴ በምጣድ ዳቦ ጋገረች፡፡

5. ሲኒ፡- ......................................................

6. ሹካ፡- ...........................................

7. ብርጭቆ፡- .............................................

8. ማማሰያ፡- .............................................

## ትምህርት ስምንት

## ምግቦችን በየምድባቸው መለየት

1. ***ማነቃቂያ፡-*** መምህር ተመጣጣኝ ምግብ ለሃይልና ሙቀት፣ በሽታ ለመከላከል፣ አካልን ለመገንባት ይጠቅማል፡፡

2. **አቅርቦት፡-** መምህር/ት ቀጥሎ የቀረበውን የምግብ አይነቶች ሃይል ሰጪ አካል ገንቢ በሽታ ተከላካይ ናቸው ፡፡አቀማመጣቸው የተዘበራረቀ በመሆኑ በየምድባቸው አስተከክለው እንዲያስቀምጡ ያድርጉ፡፡ በዛው የምግቦቹን ጥቅም ሊረዱት ይችላሉ፡፡

እንቁላል አሳ ሥጋ ፡ ማር ፡ ዳቦ ፡ በቆሎ ፡ ካሮት ፡ ፍራፍሬ ፡ ሰላጣ ፡፡

3. ***መልመጃዎች፡-*** መ/ር ከላይ የተጠቀሱትን የምግብ አይነቶች በየምድባቸው በዝርዝር አስቀምጠዋል አሁን ደግሞ ከጥቅማቸው አንጻር እንዲያስቀምጡ ያድርጉ፡፡

1.ሃይልና ሙቀት ሰጪ፡- ማር ፣ ዳቦ እና በቆሎ

2. ሰውነት ገንቢ ፡- እንቁላል ፣ አሳ ፡ ስጋ

3. በሽታ ተከላካይ ፡- ካሮት ፣ፍራፍሬ ፡ ሰላጣ

## ትምህርት ዘጠኝ

## ሥዕሎችን ከመግለጫ ጋር አዛምድ

1. **ማነቃቂያ፡-** መምህር/ት ተማሪዎች እንዲነቃቁልዎት ቀጥሎ የቀረበውን መዝሙር እርስዎን በመከተል ይዘምሩ፡፡

ጨረቃ ድቡል ቡቃ'

አጼ ቤት ገባች አውቃ፡፡

አጼ ቤት ያሉ ልጆች'

ፈተጉ ፈታተጉ'

ቁልፊቷን አስቀመጡ፡፡

ቁልፊቷ ስትሰበር፡

በዋንጫ ገለበጡ፡፡

አጃ ቆሎ ስንዴ ቆሎ

ይችን ትተሽ ይችን ቶሎ፡፡

2. **አቅርቦት፡-** መምህር ተማሪዎች የቀረበውን ሥዕል በሚገባ ከተመለከቱ በኋላ ሥዕሎቹን በሚመለከት የቀረበውን መግለጫ ጋር ያዛምዱ፡፡

1.ተማሪዎች የባንዲራ ስርዓት እያከበሩ ነው፡፡

2. ርዕሰ መምህሩ የተጣሉ ተማሪዎችን እያስታረቁ ነው፡፡

3. የጤና ባለሙያዎች የማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡

4. የጽዳት ሰራተኞች አካባቢን አፀዱ፡፡

**መልመጃዎች፡-**

1. የባንዲራ ስርዓት እንዴት ይከበራል፡   በሰልፍ
2. አካባቢ መቼ ይጸዳል፡     በጠዋት ሁል ጊዜ
3. ርዕስ መምህሩ ምን አደረጉ   ፡ተማሪዎችን አስታረቁ፡፡

# ትምህርት አስር

## ዐ.ነገር መመሥረት

1. **ማነቃቂያ** ፡-መምህር ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረበውን እንቆቅልሽ በሚገባ በማደመጥ እርስበርስ ተለማመዱ

   አዳምጡ ፡-ጠያቂ   መላሽ

   - እንቆቅልህ   ምን አውቅልህ
   - ስሄድ አገኘኋት ስመለስ አጣኋት ፡፡**ጤዛ**
   - የመሳሰሉትን እንቆቅልህ በመጠየቅ እንዲሰሩ ያድርጉ ፡፡

2. **አቅርቦት፡-** መምህር ምሳሌውን መሠረት በማድረግ ዐ.ነገር እንዲሰሩ ያድርጉ

   1. ገፈፈ ፡ ከበደ  የበሬውን ቆዳ ገፈፈ፡፡
   2. በላ ፡ ዋእሚካ ምሳውን በላ፡፡
   3. ጠጣ፡   ወንድሜ ቀዝቃዛ ውሃ ጠጣ ፡፡
   4. ወረዳ ፡ አለሙ ከስልጣን ወረደ፡፡

3. **መልመጃ** ፡-መምህር/ት ተማሪዎች በቀረበው ምሳሌ መሠረት ዐ.ነገር ይስሩ

   **ምሳሌ፡-** ነጋዴ ሽምሱ ጎበዝ ነጋዴ ነው፡-

   2. ጎረሰ-------------------------------------------
   3. ፈጣን------------------------------------------

4. ቆሻሻ ------------------------------------------
5. ንፁህ-------------------------------------------
6. አዝጋሚ----------------------------------------

በዚህ አይነት ዐ.ነገር በመስራት ይለማመዱ ፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ርዕስ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ

**ተማሪዎች ፡-** ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ

- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ይሠራሉ፡፡
- ቁጥሮችን ይጽፋሉ፡፡
- የቤተሰብ ሁኔታቸውን በጽሑፍይገልጻሉ፡፡
- ያዳመጣችሁትን ታሪክ ከገፀ ባህሪያት ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- አቅጣጫዎችን በመጠቀም ያሳያሉ፡፡
- ስለሙያ ዓይነቶች ይገልፃሉ/ይዘረዝራሉ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ ወቅቶችን ለይተው ይጠራሉ፡፡
- የጎደሉ ቃላትን በተገቢው ቃላት አሟልተው ይፅፋሉ፡፡
- አረፍተ ነገር መስርተው ያሳያሉ፡፡

### ትምህርት አንድ

### አዳምጦ መመለስ

ምንባቡን በማዳመጥ የአትክልትን ጥቅም ይናገራሉ፡፡

**1. ማነቃቂያ፡-** መምህር እባክዎ ተማሪዎች የሚወዱትን የፍራፍሬ ዓይነት ይጠይቋቸው

**2. አቅርቦት፡-** መምህር/ት እባክዎ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን" የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ዓይነቶችና ጥቅማቸው" የሚለውን ምንባብ ለተማሪዎች ያንብቡላቸው በመሃሉም ተማሪዎቹ እየተከታተሉ መሆኑን ለማወቅ አጫጭር ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

**3. መልመጃዎች፡-** በምንባቡ መሠረት የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎች ሲመልሱ እያዳመጡ የማጠቃለያ ሃሳብ ያቅርቡ

1. አትክልትና ፍራፍሬ

ቅጠላቸው ይበላል ለምሳሌ፡ የአበሻ ጎመን ፡ ጥቅል ጎመን ፡ ቆስጣ ፡ የመሳሰሉት ቅጠላቸው ይበላል

2. ፍሬያቸው የሚበሉ የጓሮ አታክልት ብርቱካን፡ ሙዝ ፡ ፓፓያ፡ ማንጎ፡ መንደሪን እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

3. የፍራፍሬ ዘሮች የሚባሉት ሙዝ ፡ ብርቱካን ፡ መንደሪን ፡ ፓፓያ....

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

**ዓላማ፡** ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች አጭር ምንባብ ያነባሉ ፡፡

<u>1. ማነቃቂያ፡-</u> መምህር/ትእባክዎ ተማሪዎቹ ምን ዓይነት ምግብ እንደሚወዱ እያሥነሱ ይጠይቋቸው፡፡

<u>2. **አቅርቦት**</u> ፡- መምህር/ት ተማሪዎቹን"እኔ ማነኝ" የሚለውን ምንባብ ከተማሪ መጽሐፍ እንዲያነቡ ይርዷቸው ፡፡ በሚያነቡበት ጊዜ የሚጠሩ የፊደል ግድፈት ካለም እያስተካከሉ እንዲያነቡ ማስተካከያዎች እየሰጡ አጠናክሯቸው፡፡

**መልመጃ**፡- ከታች በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ተማሪዎች አረፍተ ነገር ጻፉ

<u>**ምሳሌ**</u> ፡- ዘር --- አርሶ አደሩ ዘር ዘራ

1. ሙዝ
2. ቅጠል
3. ቆስጣ
4. ሰላጣ
5. ቀይስር

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

**1. ማነቃቂያ፡-** መ/ር ተማሪዎቹ የሚያናከናውኗቸው ነገሮች ሁሉ ደረጃና ቅደም ተከተል እንዳላቸው በመግለጽ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡

**2. አቅርቦት፡-** መምህር/ት በመጀመሪያ ለተማሪዎች መሳሌዎችን ይስሩላቸው ለምሳሌ፡ ከላይ በማነቃቂያ እንደተመለከቱ ምሳሌውን ያብራሩላቸው፡፡

**ምሳሌ**፡ ሰው — ይወልዳል - ያድጋል — ይሞታል


1. በቅደም ተከተል ጻፉ


   1. ቁርስ መብላት
   2. እጅን ፡ በውሃና ሣሙና መታጠብ
   3. ወደ መፀዳጃ ቤት መሄድ
   4. በጠዋት መነሳት

በጠዋት መነሳት ወደ መፀዳጃ ቤት መሄድ እጅን በውሃና በሣሙና መታጠብ ቁርስን መብላት፡፡

**3. መልመጃዎች፡-** መምህር ነገሮችን ሲያከናውኑ ያለውን የድርጊት ቅደም ተከተል በሚገባ ይንገሯቸው መልመጃውን

ያሰሯቸው ፡፡




## ክፍለ ትምህርት አራት ፡ ቁጥሮችን መጻፍ

1. **ማነቃቂያ፡-** መምህር/ት ተማሪዎችን ቁጥሮችን ወደ አሃዝ እንዲለውጡ ያድርጉ፡፡

2. በተማሪው መጽሐፍ ላይ የተሠጡ ቁጥሮች እንዲያሟሉ እስከ — 100 (፻) ያሉትን ቁጥሮችን ወደ ሆሄያት እንዲቀይሩ ያድርጉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 (፩) | አንድ | 10 (0) | አሥር |
| 2 (፪) | ሁለት | 20 (፳) | ሃያ |
| 3 (፫) | ሦስት | 30 (፴) | ሠለሳ |
| 4 (፬) | አራት | 40 (፵) | አርባ |
| 5 (፭) | አምስት | 50 (፶) | ሃምሳ |
| 6 (፮) | ስድስት | 60 (፷) | ስልሳ |
| 7 (፯) | ሰባት | 70 (፸) | ሰባ |
| 8 (፰) | ስምንት | 80 (፹) | ሰማንያ |
| 9 (፱) | ዘጠኝ | 90 (፺) | ዘጠና |
| | | 100 (፻) | መቶ |

3. መምህር ተማሪዎች በአሀዝ የተጻፉ ቁጥሮች ወደ ፊደል እንዲቀይሩ ያድርጉ።

## ትምህርት አምስት

## የቤተሰብን ሁኔታ መናገርና መጠያየቅ

1. **ማነቃቂያ፡-** መምህር እንደ ማነቃቂያ የአንድ ቤተሰብን ሁኔታ በዝርዝር ይንገሯቸው።

2. **አቅርቦት፡-** መምህር/ት ተማሪዎችን በጥንድ በጥንድ እንዲቀመጡ ያድርጉ እርስ በርስ ስለቤተሰባቸው ሁኔታ ይነጋገሩ እርስዎም ውይይታቸውን በሚገባ ይከታተሉ ሞዴል የሚሆኑ ተማሪዎችንም በማሥነሳት እንዲጠያየቁ ያድርጉ፡፡

ተማሪ 1. ስምህ ማነው?

ተማሪ 2. መጩ

ተማሪ 1. ያባትህ ስም

ተማሪ 2. ሽኩር

ተማሪ 1. ስንት ወንድሞች አሉህ?

ተማሪ 2. ሦስት ወንድሞች አሉኝ

ተማሪ 1. እህቶችስ

ተማሪ 2. ሁለት እህቶች አሉኝ

ተማሪ 1. አመሰግናለሁ፡፡

በመልመጃዎች ተማሪዎች ተመሳሳይ ምልልስ እንዲያደርጉና እቤታቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲለማመዱ ያድርጉ ይህም የመናገር ክህላቸውን ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

## ትምህርት ስድስት

## ስድስት አንብቦ መረዳት

1. **ማነቃቂያ፡-** መምህር/ት ትምህርቱን ከመጀመርዎ አስቀድመው ያለመማር ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ለተማሪዎች ይንገሯቸው ተማሪዎችንም ምን አይነት ግንዛቤ እንዳላቸው ይጠይቋቸው፡፡

2. **አቅርቦት፡-** መምህር በአቅርቦት ስር የቀረበውን ምንባብ ለተማሪዎች ከማቅረባቸው በፊት ስለተመጣጣኝ ምግብ ጠቀሜታ ይንገሯቸው በታቸለ መጠን ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት ቁርሳቸውን በሚገባ መመገብ እንዳለባቸው ይንገሯቸው በማስከተልም ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ምንባብ ያንብቡላቸው፡፡

ምንባቡን በሚገባ መረዳታቸውን ለማወቅ የተወሰነ መልዕክቶችን ካነበቡ በኂላ ቆም እያደረጉ ምን ተከሰተ እያሉ ይጠይቋቸው ፡፡ እንዲያነቡም ይጋብዟቸው ምንባቡን ካጠናቀቁ በኂላ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

**<u>መልመጃዎች፡-</u>**

1. "ተረኛ" ተረኛ" ያለው ማነው? ወ/ሮ አልማዝ
2. ዶ/ር ምን ጠየቁ ምኑን ነው ያመመው?
3. ወ/ሮ አልማዝ ምን ብለው መለሱ ሆዱ ተነፍቷል፡፡
4. ችግሩ ምን ብለው አስረዱ ወተት ፡ እንቁላል ፡ ማር ፡ አትክልትና ፍራፍሬ ይመገቡ
5. ወ/ሮ አልማዝ በምን አለቀሱ ልጄን በምግብ እጥረት ገድዬው ነበር በማለት አለቀሱ ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሰባት

### አቅጣጫን መግለጽ


1. ***ማነቃቂያ*** ፡- መምህር/ት ተማሪዎች እንዲነቃቁ ያድርጉ አቅጣጫን የሚገልጽ ሥዕል ያሳዩአቸው፡፡ ሰሜን

ምስራቅ ምዕራብ

ደቡብ -

በቦርድ ይስሉና ያሳዩአቸው፡፡

4. **አቅርቦት፡-** መምህር/ት በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የቀረበውን ሥዕል በሚገባ እንዲያዩና ከመንገድ በስተግራ በስተቀኝ ያለውን እንዲሁም ከላይና ከታች የሚጠቁመውን እንዲሁም ት/ቤት ከቤተክርስቲያን በየትኛው አቅጣጫ እንደሚገኝና በሱቅና በመስጊድ መካከል ያለውን ርቀት ያስረዷቸው፡፡



**3. መልመጃዎች፡-** መምህር/ት በሥዕሉ የተገለጸውን አቅጣጫ መነሻ ባደረገ መልኩ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡ አቅጣጫውን በሚገባ በማሳየት መልሱን ይጠይቋቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ስምንት

## ስለሙያ አይነቶች መዘርዘር

**1. ማነቃቂያ፡-** መምህር እያንዳንዱን የሙያ አይነት በዝርዝር ይንገሯቸውና እነሱም እንዲናገሩ ያግዟቸው ስለሚወለዱት የሙያ አይነትም ይጠይቋቸው፡፡

**2. አቅርቦት፡-** መምህር/ት ለተማሪዎች ከታች የቀረቡትን ሥዕሎች በሚገባ እንዲረዱ ያግዟቸው ሥዕሎቹ እያንዳንዱን የሙያ አይነት የያዙ በመሆናቸው ሥዕሉን ከመግለጫው ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡

1. ፖሊስ
2. መምህር
3. ሐኪም
4. ባንባ ሠራተኛ
5. ገበሬ ናቸው

**3. መልመጃዎች፡-** መምህር/ት በመልመጃዎቹ የቀረቡት እያንዳንዱ የሙያ አይነት ምን ተግባር እንዳለው የሚያሳይ ስለሆነ ተግባሩን በጽሑፍ ይግለጹላቸው፡ :

## ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## አያያዥን ማውጣትና ወቅቶችን መለየት

1. ***ማነቃቂያ፡-*** መምህር ተማሪዎችዎ ስለ አመቱ ወቅቶች እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡ እህል የሚዘራው መቼ ነው? መቼ ይታጨዳል? መሬት መቼ ይታረሳል? የሚሉትን ይመልሱ፡፡

2. **አቅርቦት፡-** መምህር በተማሪው መጽሐፍ የቀረበውን የአመቱ ወቅቶች የሚለውን ምንባብ ካነበቡ በኋላ ለይተው እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡ በምንባቡ ውስጥ የተገለጹትን አያያዥች ቃሎች ለይታችሁ አውጡ፡፡

**እነሱም ናቸው፡፡ሲሆን፡ደግሞ፡ሌሎችም**

3. ***መልመጃዎች፡-*** መምህር ስለ አያያዥ ቃላት የተጠቀሱትን ለይታችሁ አውጡ የሚለው ከላይ ተጠቅሰዋል፡፡

**ወቅቶችን በሚመለከት የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ይርዷቸው**

1. የበጋ ወቅቶች ታህሳስ፣ጥር እና የካቲት
2. የበልግ ወቅት መጋቢት፣ሚያዝያ እና ግንቦት
3. የክረምት ወቅት ሰኔ፣ሐምሌእና ነሀሴ
4. የፀደይ ወቅት መስከረም፣ጥቅምት እና ህዳር በማለት ያስተካክሉ፡፡

# ትምህርት አስር

## ዐ.ነገርን መመሥረት

**1. ማነቃቂያ፡-** መምህር/ት ተማሪዎች ከእንቅልፍ እንደተነሱ ስለሚያከነውኑት ተግባር ለጓደኞቻቸው እንድናገሩ ያድርጉ፡ ከዚያም አንድ ተማሪ በማሥነሳት ዐ.ነገር እንዲሰራ ያድርጉ፡ ዳንጊሶ ከመቀመጫው ተነሳ፡፡

**2. አቅርቦት** ፡- መምህር ከታች ተማሪዎች ዐ.ነገር እንዲሰሩ ምሳሌዎችን አሷዩአቸው፡፡

1. አጠበች ፡ ኡሚ ልብስ አጠበች
2. ተነሳ ፡ ሎዲስ ከእንቅልፉ በጊዜ ተነሳ
3. ደመረ ፡ ሄሊሴ ትምህርት ጀመረች
4. ተከለች ፡ ነፃነት ድንች ተከለች

**3. መልመጃዎች፡-** መምህር ተማሪዎች በተማሩት መሠረት መልመጃዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

1. ጨለመ ፡ ዛሬ ቀኑ ቶሎ ጨለመ
2. ዘነበ ፡ ዝናቡ በጣም ዘነበ
3. ሄደ ፡ መምህሩ ወደ ቢሮ ሄደ
4. አባረረ ፡ ጥበቃው ውሻውን አባረረ
5. ነገረ ፡ ተማሪው ከመምህሩ የሰማውን ለጓደኞቹ ነገረ

## ምእራፍ አስር

## ተላላፊ በሽታዎች

### ተላላፊ በሽታዎች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ታሪክን በማዳመጥ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡
- ቃላትን በማጣመር ሀረጋትንት ይመሰርታሉ፡፡
- ሁነቶችን በቅደም ተከተል በማስተካከል ያስቀምጣሉ፡፡
- ራሳችሁን የሚገልጽ ጽሑፍ ያዘጋጃሉ፡፡
- አንደኛ መደብ፣ ነጠላና ብዙ ተውላጠ ስሞችን ይለያሉ፡፡
- በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

# ትምህርት አንድ

## በሽታን ስለመከላከል መናገር

1. ማነቃቂያ ፡- በሽታ ምንድነው? ሰውን በሽታ እንዴት ሊይዘው ይችላል? ሰው በሽታን እንዴት ይከላከላል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
2. አቅርቦት፡- መምህር/ት በቅርበት በሽታን መከላከል እንዴት እንደሚቻል ጸጉርን ገላን እጅን በመታጠብ የተስቦ በሽታን መከላከል እንደሚቻል እንዲሁም ቆሻሻን በማቃጠል ዓይነምድርን በመጸዳጃ ቤት በመጠቀም የዓይን ማዝና የጉንፋን በሽታን መከላከል እንደሚቻል እንዲሁም ኩሬዎችን በማድረቅ የወባ በሽታ መቀነስ ይቻላል፡፡
3. መልመጃዎች፡- መምህር/ት ተማሪዎች በሚገባ ምንባቡን እንዲያነቡ በማድረግ ከምንባቡ የወጡትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ ያድርጉ ጥያቄዎቹም
    1. የተስቦ በሽታን እንዴት መከታተል ይቻላል፡- ጸጉርን፣ ገላንና እጅን በመታጠብና ልብስን በማጠብ
    2. የዓይን ማዝ የጉንፋን በሽታን ለመከላከል ምን ማድረግ ይገባናል፡ ፡ ዓይነ ምድርን በሽንትቤት በመጠቀም ሽንት ቤትን በመዝጋት
    3. የወባ ትንኝ እንዴት ትራባለች ውሃን አቁረው በሚያስቀሩ ቦታዎች አማካይነት፡፡

# ትምህርት ሁለት

**የሀረግ ምሥረታ**

ዓላማ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ቃላትን በማጣመር ሀረጋትን ይመሰርታሉ

**ማነቃቂያ**

ተማሪዎች ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ከ"ቤት" ጋር ያጣምሩ

**ለምሳሌ**

| ቃል | ሀረግ | |
|---|---|---|
| ማዕድ | | ማዕድ ቤት |
| ማረሚያ | **ቤት** | ----------------- |
| መኝታ | | ---------------- |
| ዳቦ | | ----------------- |
| ሥጋ | | -------------- |
| ምግብ | | -------------- |
| አቅርቦት | | -------------- |
| ማስታወሻ | | -------------- |

ሀረግ ማለት ትርጉም ያላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት መዋቅር ሲሆን ‹‹ሀረግ›› የሚለውን ስያሜ ሊያገኝ የቻለው አግባብነት ያላቸው ቃላት ተያይዘው በመርዘም ሀረግ ስለሚያስመስሉት ነው

**ምሳሌ፡-**

1. ቆንጆ ምን
2. በመምህሩ መጨረሻ
3. የመኪና ማቆያ
4. የትራፊክ መብራት

ቃላትን በማጣመር ሀረግ እንዲመሰርቱ ያድርጉ

1. መኪና ተራ                3. ሞተረኛ -- ልጅ

2. ለመሄድ ---- ወጣ        4. ቀዩ --- አስተናጋጅ

# ትምህርት ሶስት

ዓላማ፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ያደመጡትን ታሪክ በቅደም ተከተል ያዳምጣሉ

**ማነቃቂያ፡-** መምህሩ የተዘጋጀውን ምንባብ ለተማሪዎቹ ያንብቡላቸው

**እረኛውና ዋሽንቱ**

ከዕለታት አንድ ቀን እረኛው በጠዋት ተነሳዋሽንቱን ያዘ፡፡ ከብቶቹን እየነዳ ወደ ተከለለላቸው የግጦሽ ቦታ ሄደ፡፡ ከብቶቹን አሰማራና ዋሽንቱን መንፋት ጀመረ በፍጥነት አንድ በሬ ከበቆሎ ማሳ ገባበት፡፡ እረኛው ቢሮጥ አልደርስበት አለ፡፡ ዋሽንቱን ወደ በሬው ወረወረው፡፡

አቅርቦት፡- መ/ር ከዚህ በታች ያሉትን የተዘበራረቁ ዐ.ነገሮች ሁነቱን በማስተካከል እንዲማሩ ተማሪዎችን ይርዷቸው፡፡

ከታች ሰባት የተለያዩ ሀሳቦች ቀርበዋል እነዘዚህን ዐ.ነገሮ በትክክለኛው ቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡

መልመጃዎች፡- በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ሁነቶችን አስተካክሉ (ሀሳቦቹ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ)

ምሳሌ፡-

1. ከዕለታት አንድ ቀን እረኛው በጠዋት ተነሳ፡፡
2. ዋሽንቱን ያዘ፡፡
3. --------------------------
4. --------------------------
5. --------------------------
6. -------------------------
7. -------------------------

# ትምህርት አራት

## ሥርዓተ ነጥብ

**ዓላማ**፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ ይጠቀማሉ

**ማነቃቂያ**፡- መምህር ለተማሪዎቹ ስርዓተ ነጥብን በተመለከተ ገለጻ ያድርጉላቸው፡ ለምሳሌ (፡ ፡፡ ? ፣) ምን እንደሆኑ ይግለጹላቸው፡፡

አቅርቦት፡- መምህር በተማሪዎች መጽሐፍት ያሉትን ዐ.ነገሮች ተማሪዎቹ በአግባቡ እንዲያነቡና ሥርዓተ ነጥቦችን እንዲለዩ ያድርጉ

1. አበበ ትምህርቱን ያጠናል
2. መምህራችን ወደ ክፍላችሁ ግቡ አሉን
3. አባትና እናት የቤተሰብ ኃላፊዎች ናቸው
4. ተማሪዎች ለመ/ራን ታማኞች ሁኑ
5. መምህራን ለተማሪዎች አሳቢዎች ሁኑ ከ1-5 ባሉት ዐ.ነገሮች አገልግሎት ውስጥ ገብተዋል፡፡

**መልጃዎች**

ሁለት ነጥቦችን በደብተራችሁ ጻፉ

1. ሁለት ነጥብ ለምን ያገለግላል
2. በጽሁፉ ውስጥ ሁለት ነጥብ ባይኖር ምን ችግር ያጋጥማል
3. ሁለት ነጥብን በትክክለኛ ቦታ አስገቡ
4. የያዙ ሦስት ዐ.ነገሮችን ሥሩ

# ትምህርት አምስት

## ተውላጠ ስሞችን መለየት

1. ማነቃቂያ መምህር/ት ተማሪዎችን በማሥነሳት አሱን ጥራው ጥሪው እሷን አሥነሳት በማለት በስም ምትክ ለአንደኛና መደብ ነጠላ ስምና ስለ ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥሮች ይጠይቋቸው፡፡
2. አቅርቦት መምህር/ት በተማሪው መጽሐፍ የቀረበውን ማብራሪያ በሚገባ ይግለጹላቸው፡፡ ተውላጠ ስም የስም ምትክ እንደሆነ ያስረዷቸው፡፡
   1. መደብ ነጠላ ቁጥር ሲሆን እኔ፣ ብዙ ቁጥር ሲሆን እኛ
   2. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ሲሆን አንተ እንዲሁም አንቺ፣ ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር እናንተ በማለት በተግባር ያሳዩአቸው፡፡
3. መልመጃዎች

   መምህር/ት በተማሪ መጽሐፍ ስለተውላጠ ስም አንደኛ መደብ ነጠላና ብዙ ቁጥር ተምረዋል፡፡ ከላይ በተማሩት መሠረት ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
   1. እኔ የሚለው ተውላጠ ስም አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ነው፡፡
   2. አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ደግሞ ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥርን የሚያመለክት ነው፡፡

## የአራት ነጥብ (።) የነጠላ ሰረዝ (፣) ጠቀሜታ

1. ማነቃቂያ መምህር ወደ እለቱ ትምህርት ከመግባትዎ በፊት ባለፈው ክፍለ ትምህርት ስለ ሁለት ነጥብን ተምረዋል ሁለት ነጥብ ለምን እንደሚያገለግል እንዲናገሩ ያድርጉ በማስቀጠልም የእለቱን ትምህርት ርዕሰ ጉዳይ ያስተዋውቋቸው።
2. አቅርቦት፡- መምህር/ት ቀጥሎ በቀረበው ዓ.ነገሮች የተለያዩ (።) (፣) ስርዓተ ነጥቦች ቀርበዋል። ይህንንም ሊያጠናክሩ የሚችሉ ምሳሌዎች ቀርበዋል በቦርድ ላይ እንጽፉ በምሳሌ በማረዳት ያሳዩአቸው።
3. መልመጃዎች ፡- ሥርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ አስገቡ የሚል ነው የቀረቡት ጥያቄዎች
    1. አቶ ገመዳ ቤታቸው በጣም ንጹህ ነው። ግቢያቸውም ንጹህና በአበቦች ያጌጠ ነው። አቶ ገመዳ በግቢያቸው ዙሪያ ጥሩ ዛፎችን ተክለዋል።
    2. ደንድር፣ ከድር፣ ዋሚሻና ደራዴ ወላጆጃቸውን ይረዳሉ።
    3. ታላላቅ ወንድሞቼ አበበ፣ ፈለቀ፣ በለጠና መንግስቱ ናቸው በሚል ያስተካክሉ።

# ክፍለ ትምህርት ስድስት

## ወገን ለወገን

### 4. ማመጥና መናገር

ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ለተማሪዎች

**ማነቃቂያ፡-**

መ/ር እባክዎ በመምህሩ መምሪያ ያለውን "ቀይዋ ወፍ" የሚለውን ምንባብ ከተማሪ መጽሐፍ ላይ ያንብቡላቸው

**አቅርቦት፡-**

5. በመቀጠልም "ፍትህ ምንድነው" የሚለውን ምንባብ ከተማሪው መጽሐፍ ላይ ያንብላቸው ተማሪዎቹም በአግባቡ መከታተላቸውን ለማረጋገጥ መሐል ላይ ሲደርሱ ቆም ብለው ይጠይቋቸው፡፡ የታሪኩ ቀጣይ ሀሳብም ምን ሊሆን ይችላል የሚለውን እንዲገምቱ ያድርጉ በመጨረሻም የጀመሩላቸውን ምንባብ ይጨርሱ፡፡
6. መልመጃዎች
7. ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ተማሪዎቹን ይጠይቁ ተማሪዎቹም በቃል ይመልሱ

# ትምህርት ሰባት

## የዐ.ነገር ምሥረታ

1. ማነቃቂያ መምህር/ት ባለፈው ዕለት ስለተማሩት ይጠይቋቸው እነሱም ስለ ጥያቄ ምልክት ነው የተማርነው ጠቀሜታዉን ጥያቄዊ ዐ.ነገር ለመግለጽ ነው በማስከተልም የዕለቱን ትምህርት ምን እንደሆነ በመንገር በቃላቸው ዓ.ነገር እንዲመሰርቱ ያድርጉ
2. አቅርቦት መምህር/ት ዐ.ነገርን በሚመለከት ማስታወሻ ይስጧቸው በመቀጠልም ማብራሪያዎችን በማከል ርዕሰ ጉዳዩን ያዳብሩላቸው በማስከተል የዐ.ነገር አይነቶችን ይዘርዝሩላቸው

   ሐተታዊ ተራ፡ ዐ.ነገር ታፈሰ ሳር አጨደ፡፡

   ጥያቄያዊ ዕድሜህ ስንት ነው?

   1. ትዕዛዛዊ ከጓደኛህ ጋር አጥና!
3. መልጃዎች ፡ መምህር/ት ተማሪዎች ዐ.ነገር መስራትን ያለማዷቸው
   1. **በላ** አስማረ ምሳውን በላ፡፡
   2. **ጎበዝ** አያና ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡
   3. **ገባ** አቤል በሦስት ዓመቱ ትምህርት ቤት ገባ፡፡

## ጥያቄ ምልክት

1. ማነቃቂያ መምህር/ት ተማሪዎቹን ለማነቃቃት ባለፈው የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያድርጉ በማስከተልም ጥያቄ መልክት ደግሞ የእለቱን ትምህርት ትኩረት እንደሆነ ይንገሯቸው፡፡
2. አቅርቦት መምህር/ት በዚህ ክፍል ከስርዓተ ነጥቦች መካከል ሊረዱት ይገባል ተብሎ የሚታሰበው የጥያቄ ምልክት ቀርቧል፡፡ ስርዓተ ነጥብም በሀረግ እንዲሁም በዓ.ነገር በመዋቀር በምሳሌ ተብራርቶ

ተቀምጧል። የጥያቄ ምልክት ለጥያቄያዊ ዐ.ነገር መቋጫነት እንደሚያገለግል በሚገባ ይንገሯቸው።

3. መልጃዎች መምህር/ት የቀረቡትን መልመጃዎች በእርስዎ መሪነት እንዲሰሩ ያድርጉ ካጠናቀቁ በኋላ ያርሙላቸው።

የቀረቡት ጥያቄዎች

1. ወደ ትምህርት ቤት ምን ይዘህ መጣህ?
2. አባትህ ለበአል ምን ገዙልህ?
3. በየጊዜው ገላችንን የምንታጠበው ለምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ይስሩላቸው።

## ክፍለ ትምህርት ስምንት

### መጻፍ

**ዓላማ**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች እራሳቸውን የሚገልጽ ጽሑፍ ይጽፋሉ

**ማነቃቂያ፡-** መምህር ተማሪዎቹን ባለፈው ስለተማሯቸው ትምህርቶች ይጠይቋቸው ተራ በተራ በቃል እንዲገልፁ ያበረታቷቸው።

**አቅርቦት፡-**ተማሪዎቹ ቃላትን በማቀናጀት እራሳቸውን የሚገልጽ ዐ.ነገር እንዲሰሩ ያግዟቸው። በመጀመሪያ ይለማመዱ በቃላቸውም ይግለጹ እርስበርስ ከተወያዩ በኋላ እንዲጽፉ ያድርጉ።

**መልመጃዎች**

መ/ር በአቅርቦት ላይ የቀረቡትን ሙከራዎች እንዲያደርጉ አግዘዋል፡፡ ያገኟቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡ የቤተሰቡን ሁኔታ እና የራሳቸውን ሁኔታ እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡

ሞዴል ተማሪዎች በማሥነሳት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | የክሒልዓይነቶቹ | ውጤት/ዓላማ | ይዘት | የማስተማር ዘዴ | ምዘና | ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ማዳመጥ | ➢ የንግግር ድምጾችን ይለያሉ።<br>➢ ድምጾችን ይጠራሉ፣ ይለያሉ።<br>➢ ሆሄያትን በየቅርጻቸው ይለያሉ።<br>➢ ያዳመጡትን ቃላት በትክክል ይጠራሉ።<br>➢ ያዳመጡትን ለይተው ያሳያሉ።<br>➢ ያዳመጡትን በሥዕል | ➢ የንግግርድምጾች<br>➢ ድምጾች<br>➢ ሆሄያትን መለየት<br>➢ ቃላትን አዳምጦ መናገር<br>➢ አዳምጦ ነገሮችን ማሳየት<br>➢ አዳምጦ መሳል | ➢ በጋራ በመሆን ድምጾችን በመጥራት፣ በማዳመጥ።<br>➢ በመቅረጸ ድምጽ(ቪዲዮ)የተደገፉ መዝሙሮችን በማዳመጥ።<br>➢ ሆሄያትን(ፊደላትን)(ፍላሽ ካርድ) በቅርጸ ቅርጽ መልክ በማዘጋጀት<br>➢ የግል ስራ<br>➢ አሳታፊ አቀራረብ<br>➢ ሰርቶ ማሳየት<br>➢ የሚና ጨዋታ | ➢ ምልከታ<br>➢ ምልከታ<br>➢ የቃል ምላሽ<br>➢ ምልከታ<br>➢ ምልከታ<br>➢ ክትትል<br>➢ የቤ.ጤ እርማት<br>➢ ምልከታ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ያሳያሉ፡፡<br>➢ ያዳመጡትን የቃል መመሪያ ይተገብራሉ፡፡<br>➢ ያዳመጡትን አስተካክለው ያስቀምጣሉ፡፡<br>➢ ያዳመጡትን ታሪክ ከገጸባህርያት ጋር ያዛምዳሉ፡፡<br>➢ በክፍል ውስጥ አቅጣጫዎችን ያሳያሉ፡፡<br>➢ ከታሪኩ ለተውጣጡ ጥያቄዎች የተረዱትን ይመልሳሉ፡፡ | ➢ አዳምጦ መከወን<br>➢ ያዳመጡትን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ<br>➢ አዳምጦ ማዛመድ<br>➢ አቅጣጫዎች<br>➢ ውስን ታሪክ | ➢ ውይይት<br>➢ ትረካና የቡድን ስራ<br>➢ አካላዊ ምላሽ<br>➢ ጥያቄና መልስ | ➢ ታሪክን መናገር<br>➢ አቅጣጫ ማሳየት<br>➢ አጭር መልስ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2. | መናገር/ንግግር | ➢ ፊደላትን ይጠራሉ፡፡<br>➢ መዝሙር ይዘምራሉ፡፡<br>➢ ፊደላትን በማጣመር ቃላትን ይናገራሉ፡፡<br>➢ በሰላምታ እራሳቸውን ይገልጻሉ፡፡<br>➢ ነጻ ውይይት ያደርጋሉ፡፡<br>➢ በተለያዩ አውዶች አዳዲስ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡<br>➢ ቁጥሮችን በአሀዝ ያሳያሉ፡፡<br>➢ መሰረታዊ ቃላትን ይናገራሉ፡፡ | ➢ ፊደል<br>➢ መዝሙር<br>➢ የፊደላት ጥምረት<br>➢ ሰላምታ<br>➢ ውይይት<br>➢ አዳዲስ ቃላት<br>➢ ቁጥሮች<br>➢ መሰረታዊና ተዘውታሪ ቃላት<br>➢ ቀለማትን መግለጽ<br>➢ የሙያ አይነቶች<br>➢ የሳምንቱ ቀናት | ➢ የግል ስራ<br>➢ የቡድን ስራ<br>➢ የተናጥል ስራ<br>➢ የቡድን ስራ<br>➢ የአቻ ውይይት<br>➢ የቡድን ስራ<br>➢ ሰርቶ ማሳየት<br>➢ ምልልስ<br>➢ ሰርቶ ማሳየት(አይ.ሲ.ቲ)<br>➢ ምልልስ<br>➢ የህብረት ስራ | ➢ አጭር ሙከራ<br>➢ ምልከታ<br>➢ የቃል ምዘና<br>➢ የአቻ ጨዋታ/ምልልስ<br>➢ የአቻ ግምገማ<br>➢ ምልከታ<br>➢ ጽብረቃ<br>➢ የቃል ምላሽ<br>➢ ሙከራ<br>➢ ማዛመድ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ➢ የቀለማት ዓይነቶችን ይገልጻሉ፡፡<br>➢ የሙያ አይነቶችን ይገልጻሉ፡፡<br>➢ በየሳምንቱ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ይገልጻሉ፡፡ | | | ➢ አጭር ሙከራ | |
| 3. | ማንበብ | ➢ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ፊደላትን ያነባሉ፡፡<br>➢ ሥዕሎችን በማየት ይገልጻሉ፡፡<br>➢ ተቃራኒ ቃላትን ያነባሉ፡፡<br>➢ ተመሳሳይ ቃላትን | ➢ ፊደላትን ማንበብ<br>➢ ስዕላዊ ገለጻ<br>➢ የቃላት ንጽጽር<br>➢ ቃላትን ማዛመድ | ➢ ጨዋታና ተግባር ተኮር<br>➢ የዕይታ ዘዴ፣ስዕላዊ ትረካ<br>➢ ይዘት ተኮር<br>➢ የቡድን ተግባር<br>➢ ውይይት/ስዕላዊ ገለጻ<br>➢ መምህር መርእና የተማሪው የግል ስራ | ➢ የቃል ንባብ<br>➢ መናገር<br>➢ ቃላዊ ንባብ፣ ምልከታ<br>➢ ድንገቴ ጥያቄ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በማዛመድ ያነባሉ፡፡<br>➢ የቃላትን አውዳዊ ፍቺ ይለያሉ፡፡<br>➢ ተዛማጅ ቃላትን ያነባሉ፡፡<br>➢ ከምንባቡ ውስጥ መረጃዎችን ፈልገው ያገኛሉ፡፡<br>➢ የተለያዩ ጽሑፎችን በማንበብ ተዛማጅ ቃላትን ያወጣሉ፡፡<br>➢ ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፡፡<br>➢ ቁጥሮችን እየጠሩ ይጽፋሉ፡፡<br>➢ ሐረጋትን በማጣመር ዓረፍተ | ➢ የቃላት ግንዛቤ<br>➢ ተዛማጅ ቃላት<br>➢ መረጃ መፈለግ<br>➢ ዓረፍተ-ነገርን ማንበብ<br>➢ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች<br>➢ ቁጥሮችን ማንበብ<br>➢ የዓረፍተ-ነገር ምሥረታ<br>➢ ሁነቶችን ማስተካከል<br>➢ ህዳግና መስመር<br>➢ የጽሕፈት | ➢ የቡድን ስራ<br>➢ መምህር መር<br>➢ ጥያቄና መልስ<br>➢ መምህር መር<br>➢ የግል ስራ<br>➢ በድግግሞሽ መግለጽ | ➢ ምልከታ<br>➢ የግል ስራ(ኢንተራክቲቭ)<br>➢ ልዩ ልዩ የመረጃ ምንጮች<br>➢ ምልከታ<br>➢ ክፈት ጥያቄዎች<br>➢ የአቻ ምዘና<br>➢ ሐረጋቱ ላይ ምልክት | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4. | ጽህፈት | ነገር ይመሰርታሉ።<br>➢ ባነበቡት ታሪክ ውስጥ ያሉትን ሁነቶች በቅደም-ተከተል ያስቀምጣሉ፡፡<br>➢ መስመርና ህዳግን ጠብቀው ይጽፋሉ።<br>➢ ሰባት ወይም ከዝያ በላይ በሆነቃልና ቃል፣ሀረግና ሀረግ መካከል ያለውን ርቀት ጠብቀው ይጽፋሉ።<br>➢ ቀለል ያሉ ቃላትን በመጠቀም የዕለት | ልምምድ<br>➢ የዕለት ተግባር<br>➢ ነጠላ ዓ.ነገር<br>➢ ጽሕፈትን መለማመድ<br>➢ አካላዊ ገጽታ<br>➢ እንሰሳት<br>➢ አካባቢ(መንደር)<br>➢ መጓጓዣ<br>➢ ዕቃዎች<br>➢ ምግብ | ➢ የግል ስራ<br>➢ ሰርቶ ማሳየት<br>➢ የግል ስራ<br>➢ የቡድን ስራ<br>➢ የማነቃቂያ ዘዴ<br>➢ በቴክኖሎጂ የታገዘ የታገዘ የማስተማር ዘዴ | ማድረግ<br>➢ ውይይት፣ ምልከታ<br>➢ ምልከታ፣ የማህደር ተግባር ምዘና<br>➢ የማሕደር ተግባር ምዘና<br>➢ የጽሑፍ ሙከራ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5. | ቃላት | ተግባራቸውን ይጽፋሉ፡፡<br>➢ ነጠላ ዓ.ነገሮችን በመጠቀም ውስን ታሪክ ይጽፋሉ፡፡<br>➢ እራሳቸውን በጽሑፍ ይገልጻሉ፡፡<br>➢ ቅጽሎችን በመገጣጠም አካላዊ ገጽታቸውን ያሳያሉ፡፡<br>➢ የእንስሳት ስሞችን ይዘረዝራሉ<br>➢ የሚኖሩበትን፣ የሚገኙበትን አካባቢ ይገልጻሉ፡፡ | ➢ ቀለማት/የትራፊክ መብራት<br>➢ ቤተ-ዘመድ<br>➢ አልባሳት<br>➢ ቤት(የቤት ክፍሎች)<br>➢ ጾታ<br>➢ ብዙ/ነጠላ ስሞች<br>➢ ተውላጠ ስም | ➢ ጥያቄና መልስ<br>➢ የቡድን ስራ<br>➢ የአቻ ውይይት<br>➢ ይቡድን ተሳትፎ<br>➢ የቢጤ ውይይት<br>➢ የቡድን ስራ፣ ቀለማትን በየዓይነታቸው ይለያሉ፡፡<br>➢ የግል ስራ<br>➢ ገለጻ<br>➢ የግል ስራ<br>➢ ጥያቄና መልስ<br>➢ የቃል ጨዋታ | ➢ የጽሕፈት ምዘና<br>➢ የጽሑፍ ፈተና<br>➢ የቢጤ ምላሽ<br>➢ ሙከራ(ቃላዊ ምላሽ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሰዋስው | ➢ የመጓጓዣ አይነቶችን ይዘረዝራሉ፡፡<br>➢ የቤት ዕቃዎችን ስማቸውንና አገልግሎታቸውን ይዘረዝራሉ፡፡<br>➢ ምግቦችን በየምድባቸው ያስቀምጣሉ፡፡<br>➢ ቅጽሎችን(ገላጭን) ተጠቅመው ቀለማትን ይለያሉ፡፡<br>➢ ቤተዘመዶቻቸውን ይጠይቃሉ፡፡<br>➢ የልብስ ዓይነቶችን ያሳያሉ፣ ይዘረዝራሉ፡፡<br>➢ የቤት ክፍሎችን | | ➢ የቢጤ ጨዋታ | ➢ ዘገባ ማቅረብ፣ አካቢን መግለጽ<br>➢ ማዛመድ<br>➢ ማዛመድ<br>➢ የቃል ጥያቄ<br>➢ ማቅለም<br>➢ ጽብረቃ<br>➢ ምልከታ | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6. | | ይለያሉ፡፡<br>➢<br>➢ ከተሰጣቸው አውድ ውስጥ የተጠቀሰውን ጾታ ለይተው ያሳያሉ፡፡<br>➢ በአውዱ መሠረት ነጠላና ብዙና ነጠላ ቁጥር ስሞችን ይጠቀማሉ፡፡<br>➢ አንደኛ መደብ ነጠላና ብዙ ተውላጠ ስሞችን ይለያሉ፡ | | | ➢ አዛምድ<br>➢ ቃላዊ ምላሽ<br>➢ ክትትል<br>➢ የተግባር ምልከታ | |

# የመማር ብቃት

| ተ.ቁ | መሰረታዊ የቋንቋ ክሒሎች | ሶስተኛ ክፍል<br>✓ ተማሪዎቹ 3ኛክፍልን ሲያጠናቅቁ ማወቅ ያለባቸው፡- |
|---|---|---|
| 1. | ❖ የደመጣ ክሒል/ ማዳመጥ | ➢ የታላሚ ቋንቋ ድምጸ ልሳናትን ይለያሉ፡፡<br>➢ በተመሳሳይ/በአንድ አይነት/ ድምጽ የሚጀምሩና በተመሳሳይ ድምጽ የሚጨርሱ ቃላትን ይለያሉ፡፡<br>➢ ተዘውታሪ ቃላትን በመጠቀም ይመልሳሉ፡፡<br>➢ የግለሰባዊ መረጃ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ<br>➢ ከጓደኞቻቸው ጋር ሰላምታ ይለዋወጣሉ፡፡<br>➢ አውዳዊ የሆኑ የሚና ጨዋታዎችን ያቀርባሉ፡፡<br>➢ ለየት ያሉ መረጃዎችን ያዳምጣሉ፡፡<br>➢ ቀለል ያሉ መመሪያዎችን ይከውናሉ፡፡ |
| | | ➢ ረዘም ያሉ ቃላትና ሐረጋትን በትክክል ይጠራሉ፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 2. | ❖ የንግግር ክሒል/ ንግግር | ➢ ተዘውታሪ ቃላትን በትክክለኛ ንበት ይጠራሉ፡፡<br>➢ ሐሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡<br>➢ ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ፡፡<br>➢ ቤተሰቦቻቸውን ያስተዋውቃሉ፡፡ |
| 3. | ❖ አንብቦ መረዳት/ ንባብ | ➢ ባለ አንድ ቀለም ቃላትን ያነባሉ፡፡<br>➢ ከ4-5 ቃላት ያሉትን ዓ.ነገሮች ያነባሉ፡፡<br>➢ ውስብስብ ቃላትን ያነባሉ፡፡<br>➢ ከሚቀርቡ ተረቶች ውስጥ ስሞችን ይለያሉ፡፡ |
| 4. | ❖ የጽሕፈት ክሂል | ➢ ፊደሎችን ይጽፋሉ፡፡<br>➢ ቀለል ያሉ ቃላትን ይጽፋሉ፡፡<br>➢ ተራ ዓ.ነገር ይጽፋሉ፡፡<br>➢ ግለ-መረጃ (ስለ ቤተሰብ) ይጽፋሉ፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 5. | ❖ የቃላት እውቀት | ➢ የሰውነት ክፍል፣የአየር ሁኔታ፣ቤተሰባዊ ዝምድናን እና ልብሶችን የሚገልጹ ቃላትን ይማማራሉ::<br>➢ መልኮችን፣ አራዊትን፣ የክፍል ውስጥ ቁሶችን እና መጓጓዣን የሚገልጹ ቃላትን ይማማራሉ:: |
| **6.** | ❖ **ሰዋስው** | ➢ እንስታይና ተባእታይ ስሞችን ይለያሉ::<br>➢ ፆታን ከግስ ጋር በማጣታም ይጠቀማሉ::<br>➢ ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን ይለያሉ::<br>➢ አንደኛ መደብ ተውላጠ ስሞችን ይጠቀማሉ::<br>➢ ስሞችን እንደቁጥራቸው ከነጠላና ከብዙ ቁጥር ግሶች ጋራ በማጣጣም ይጠቀማሉ::<br>➢ ሁለተኛና ሶስተኛ ምድብ ተውላጠ ስሞችን በነጠላና በብዙ ቁጥራቸው ይጠቀማሉ:: |

# የ3ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የይዘት ፍሰት ሰንጠረዥ

| ክሂል | | 3ኛ ክፍል |
|---|---|---|
| ማዳመጥ | ድምጾች | ድምጾችን ይሰማሉ፡፡ |
| | የንግግርድምጾች | አናባቢና ተነባቢ ድምጾችን ይለያሉ/ይጠራሉ |
| | ሆሄያት | ሆሄያትን በየቅርጻቸው ይለያሉ |
| | ቃላት | ቃላትን ማዳመጥ እና መልሶ መጥራት |
| | አዳምጦመተግበር | ሁነቶችን አዳምጦ መተግበር |
| | አዳምጦመዘመር | የዳመጡትን መልሰው ይዘምራሉ |
| | አዳምጦመከወን | ያዳመጡትን የቃል መመሪያ ይተገብራሉ |
| | ያዳመጡትንበቅደምተከተልማስቀመጥ | ትእዛዙ መሠረት ያዳመጡትን በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ |
| | አዳምጦማዛመድ | ያዳመጡትን ታሪክ ከገጸ ባህሪያት ጋር |

| | | |
|---|---|---|
| | | ያዛምዳሉ |
| | አቅጣጫዎች | በክፍል ውስጥ ያሉ አቅጣጫዎችን ያሳያሉ |
| | ውስንታሪክ | አዳምጠው ይመልሳሉ |
| መናገር/ንግግር | ፊደል | መቀላቀልና መነጣጠል/ይቀላቅላሉ፣ ይነጣጥላሉ |
| | መዝሙር | መዝሙር ይዘምራሉ |
| | የፊደላትጥምረት | ፊደላትን በማጣመር በዜማ ይጠራሉ |
| | ሰላምታ | ሰላምታ መለዋወጥ |
| | ውይይት | እርስ በእርስ ይወያያሉ |
| | ቃላት | አዳዲስ ቃላትን ይገልጻሉ |
| | ቁጥሮች | ቁትሮችን ከፊደል ጋር ያዛምዳሉ |
| | መሰረታዊናተዘውታሪቃላት | አዳዲስ ቃላትን ይጠቀማሉ |
| | ቀለማት | የቀለማትን ዓይነት ይለያሉ |
| | ሙያ | የሙያ ዓይነቶችን ይለያሉ |

| | | |
|---|---|---|
| | የሳምንቱቀናት | የሚከውኑትን ተግባር መናገር |
| ማንበብ | ፊደላት | ፊደላትን መጥራት/ማንበብ |
| | ሥዕል | ስላዊ ገለጻን ማንበብ |
| | የቃላትንጽጽር | ቃላትን ማነጻጸር |
| | ቃላትንማዛመድ | ተመሳሳይ ቃላትን ይለያሉ |
| | የቃላትግንዛቤ | የቃላት አውዳዊ ፍቺ |
| | የቃላትተዛምዶ | ተዛማጅ ቃላትን ማንበብ |
| | መረጃመፈለግ | ከምንባብ መረጃን ማውጣት |
| | ዐረፍተነገር | አረፍተ ነገርን ማንበብ |
| | አንብቦመረዳት | ከምንባቡ መረጃዎችን ማውጣት |
| | ቁጥሮች | ቁጥሮችን በአሀዝ መጥራት |
| | ሁነቶች | ያነበቡትን ታሪክ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ |
| ጽህፈት | ህዳግናመስመር | ህዳግና መስመርን ጠብቆ መጻፍ |
| | ጽህፈት | ርቀትን ጠብቆ መጻፍ |

| | | |
|---|---|---|
| | የእለትተግባር | በቀላል ቃላት የእለት ተግባርን መጻፍ |
| | ነጠላዐረፍተነገር | ነጠላ አረፍተ ነገርን በመጠቀም ውስን ታሪክ መጻፍ |
| | ጽህፈት | እራሳቸውን በጽሑፍ መግለጽ |
| ቃላት | አካላዊገጽታ | አካላዊ ገጽታን መግለጽ |
| | እንሰሳ | የቤትና የዱር እንስሳትን መዘርዘር |
| | መንደር | የመኖሪያ ቦታን መግለጽ |
| | መጓጓዣ | የመጓጓዣ ዓይነቶችን መዘርዘር |
| | እቃዎች | የቤት እቃዎችን መዘርዘር |
| | ምግብ | የምግብ ዓይነቶችን በየምድባቸው ማስቀመጥ |
| | ቀለማት/የትራፊክመብራት | ቅጽሎችን በመጠቀም ቀለማትን መዘርዘር |
| | ቤተሰብ | ቤተ-ዘመዶቻቸውን መዘርዘር/አባት፣ እናት፣አጎት፣አክስት…. |
| | አልባሳት | የልብስ ዓይነቶችን ይገልጻሉ/ቁምጣ ፣ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ሱሪ፣ሸሚዝ፣/… |
| | ቤት | የቤት ክፍሎችን መግለጽ |
| ሰዋስው | ጾታ | ወንድና ሴት ጾታን መለየት /እንስት እና ተባእት/ |
| | ስሞች | ብዙና ነጠላ ስሞችን መጠቀም |
| | ተውለጠስም | ምድብ ተውላጠ ስሞችን መግለጽ |
| | | |
| | | |